ማደሱና ከእንግዳ ነገር መጽዳቱ ደግሞ ከፍ ያለው ደረጃ ነው:: የነህምያ የመሪነት ትኩረት የእግዚአብሔር ስም ይከበር ዘንድ የፈረሰው እንዲታደስ፤ ሕዝቡ ከበደላቸው በንስሐ እንዲመለሱና የተደባለቀው እንዲጠራ ማድረግ ነው::

ለትልቅ መንፈሳዊ ሥራ ትልቅ ጠላት እንዳለው የሚያውቅ እንደ ነህምያ ዓይነት መሪ በጠላቶቹ ማባበል አይደለልም፤ ዛቻቸውንም አይፈራም፤ ይልቁን በአምላኩ በመታመን በትጋት ሠርቶ ይጨርሳል:: እንዲህ ያለ መሪ «ተጀምሮ በእንጥልጥል የቀረ ሥራ ያልተጀመረ ያህል ነው» ብሎ ስለሚያስብ በአምላኩ ታምኖ የጀመረውን ለመጨረስ ይተጋል::

ነህምያን ከሥራው ለማዘናጋት ‹ና እንገናኝ› ላሉት ሁሉ «...ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፤ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም፤ ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል?» (6:1-4) በማለት መለሰላቸው:: በእግዚአብሔር ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ከሥራው የሚያዘናጋውንና የሚገዳደረውን ሁሉ በእግዚአብሔር ታምኖ በማስወገድ የተሰጠውን ኃላፊነት ዳር ማድረስ ይጠበቅበታል:: ዓይኑን በችግሩ ላይ የሚያደርግ ሰው የተጠናቀቀ ቅጥር ማሰብ አይችልም:: የእግዚአብሔርን ትልቅነት የሚያስብ ግን ችግሩ ስለሚያንስበት በርትቶ ይሠራል::





## ምዕራፍ 6

# ጴጥሮስ

ስምዖን ይባል የነበረው ጴጥሮስ የዮና ልጅ ነው (ማቴ 16:17፤ ዮሐ 1:42):: እንድርያስ የሚባል ወንድም ነበረው (ማር 1:16):: በገሊላ ባሕር አጠገብ በሚገኘው ቅፍርናሆም ዓሣ አጥማጅ ነበር (ማር 1:21፤29):: ታንኳም ነበረው (ሉቃ 5:3):: ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ወንድሙን እንድርያስን ዓሣ ሲያጠምዱ አግኝቷቸው ከኋላው እንዲከተሉትና ሰዎችን እንዲያጠምዱ ጠራቸው (ማቴ 4:18-19፤ ማር 1:16-17)::

ጌታ ኢየሱስ ስምዖንን ሲያገኘው ‹ኬፋ› አለው (ዮሐ 1:42):: ኬፋ የአረማይስጥ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ዓለት ማለት ነው:: ‹ኬፋ› በግሪከኛ ጴጥሮስ ማለት ሲሆን ትርጉሙም ዓለት ማለት ነው:: ወንድማማቹ እንድርያስና ጴጥሮስ ከአስራ ሁለቱ የጌታ ደቀ መዛሙርት መካከል ነበሩ:: ጴጥሮስ ደግሞ ጌታ በጣም ካቀረባቸው ሦስት ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ነበር:: ጴጥሮስ ያገባ ሰው ነበር (ማቴ 8:14-15፤ ማር 1:29-31፤ ሉቃ 4:38፤ 1ቆሮ 9:5):: እንደ ፈሪሳውያን የአይሁድ ሕግን የተማረ ሰው አልነበረም (ሐዋ 4:13)::

በወንጌሎች እንደምንመለከተው ከደቀ መዛሙርት መካከል አብዛኛውን ጊዜ ስሙ ቀድሞ የሚጠራው የጴጥሮስ ነው:: ከእኩያሞች መካከል ቀዳሚ እንደ ማለት ነው:: እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ቀድሞ የሚናገር በመሆኑ ‹አፈ

ደቀ መዛሙርት› ነበር ማለት ይቻላል (ማር 1:36፤ ሉቃ 22:32)፡፡ ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ «ሰዎች እኔን ማን እንደሆንሁ ይላሉ?» ካለ በኋላ «እንናተስ?» ብሎ ሲጠይቃቸው (ማቴ 16:15) ኢየሱስ መሢሑ እንደሆነ የተናገረ ጴጥሮስ ነበር፡፡

ጌታ ኢየሱስ የበለጠ ያቀርባቸው ከነበሩ ሦስት ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ጴጥሮስ በመሆኑ ከተቀሩት የበለጠ የጌታን ድንቅ ሥራ በቅርበት ተመልክቷል፡፡ ለምሳሌ ትንሿን ልጅ ከሞት ሲያስነሣ (ማር 5:37፤ ሉቃ 8:51)፤ ጌታ መልኩ በተለወጠበት ጊዜ (ማቴ 17:1-2)፤ በጌቴሴማኒ ጌታ በሚቃትትበት ሰዓት (ማቴ 26:37፤ ማር 14:33)፡፡ እንዲሁም ጌታ ከሞቱ በፊት የመጨረሻው ሳምንት ራት እንዲያዘጋጁ ከተላኩት ሁለት ደቀ መዛሙርት አንዱ ጴጥሮስ ነበር (ሉቃ 22:8)፡፡ በተጨማሪም ሰይጣን ሁሉንም ደቀ መዛሙርት እንዲያበጥራቸው እንደለመነ ከተናገረ በኋላ ሲመለስ ግን ወንድሞችን የማጽናት ኃላፊነት የሰጠው ለጴጥሮስ ነበር (ሉቃ 22:31)፡፡

የጴጥሮስን ባሕርይ የሚያጠኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ‹ሳያስተውል የሚናገር ችኩሉ ጴጥሮስ› ይሉታል፡፡ ለሚሰማው ነገር ቶሎ መልስ ለመስጠት ይሞክራል፤ የሚያየውን ራሱ ለመሞከርና ለማረጋገጥ ይፈጥናል፡፡ ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጴጥሮስ ግን «ጌታ ሆይ፤ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ» (ማር 14:25) አለ፡፡ ከታንኳቱ ወርዶም በባሕሩ ላይ ጉዞ ጀመረ፡፡ ጌታ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርትን እግር ሲያጥብም «የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም» (ዮሐ 13:8) ያለው ጴጥሮስ ነበር፡፡ እንዲሁም በመጨረሻዋ ሰዓት «...ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም» (ማቴ 26:33) ብሎ ነበር፡፡





ጴጥሮስ ከደቀ መዛሙርት መካከል ወደ ባዶው መቃብር ለመግባት የመጀመሪያው ሰው ነበር፡፡ ከሦስት ቀናት በፊት ኢየሱስን ‹አላውቀውም› ብሎ ክዶት ነበር፡፡ በሦስተኛው ቀን ግን በማለዳ ወደ መቃብር የሄዱት መቃብሩ እንደተፈነቀለ ሲናገሩ ወደ መቃብር ለመሮጥ አልዘገየም፡፡ ወደ መቃብሩም ገብቶ ኢየሱስ በዚያ እንደሌለና ከሙታን እንደተነሣ አረጋገጠ (ዮሐ 20:1-9፤ ሉቃ 24:1-12))፡፡ እንዲሁም የተነሣውን ጌታ ለማየት የመጀመሪያው ደቀ መዝሙር ነው (ሉቃ 24:34)፤ በኋላም ጌታ ራሱ ለኬፋ ታየ (1ቆሮ 15:5)፡፡

ከጌታ ትንሣኤ በኋላ ስምዖን ጴጥሮስ ዓሣ ወደ ማጥመዱ ተመልሶ ነበር፡፡ ሌሎች ደቀ መዛሙርትም ከእርሱ ጋር ነበሩ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በባሕር ዳር ቆሞ «መረቡን በታንኳይቱ በስተ ቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ» ባላቸው ጊዜ እንደ ቃሉ አደረጉ፡፡ በዚያንም ጊዜ ሊጐትቱት እስኪያቅታቸው ድረስ ብዙ ዓሣ ያዙ፡፡ «ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን ጌታ እኮ ነው አለው፡፡ ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበረና ልብሱን ታጥቆ ወደ ባሕር ራሱን ጣለ» (ዮሐ 21:2-7)፡፡ ዓሣ ለማጥመድ ሌሎችን መርቶ የሄደው ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን ሲረዳ ያጠመደውንም ትቶ ወረደ፡፡ ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል «በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወድቆ ጌታ ሆይ፤ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ» (ሉቃ 5:8) ያለውን ያሳስበናል፡፡ ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚያውቀው ብዙ ነው፤ ያከብረዋልም፡፡

ጌታ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ «ትወደኛለህን?» ብሎ በተደጋጋሚ ከጠየቀው በኋላ «ግልገሎቼን አሰማራ ...ጠቦቶቼን ጠብቅ ...በጎቼን አሰማራ» (ዮሐ 21:15-17) ብሎታል፡፡ ጌታ ካረገ በኋላ ጴጥሮስ በመቶ ሀያዎቹ መካከል ቀዳሚ ሰው ነበር፡፡ ኢየሱስን አሳልፎ በሰጠው በይሁዳ ስፍራ ሌላ ሐዋርያ እንዲመረጥ ተናገረ (ሐዋ 1:15-26)፤ ምርጫውም ተደረገ፡፡

የባለ ኀምሳ ቀን ለጴጥሮስ፤ ለሐዋርያትና አብረው ለነበሩ ሁሉ የተስፋ ሙላት ቀን ነበር። ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋ 1:8) እንዳለው ሲጠባበቁት የነበረው ተስፋ የተፈጸመበት ቀን ነበር። ይህ ጌታ ኢየሱስ ካረገ ከአስር ቀን በኋላ ከሞት ከተነሣ ደግሞ ከሃምሳ ቀን በኋላ የሆነ አስደናቂ በረከት ነው። ከዚህ ቀን ጀምሮ ጴጥሮስ ‹ኃይልን ለበሰ›፤ ልዩ ድፍረት ተጨመረለት። በባለ ኀምሳ ቀን በጴጥሮስ ስብከት ሦስት ሺህ ሰዎች አመኑ።

ከዚያም በኋላ ብዙ ተአምራት በእጆቹ ተደርገዋል። ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነ መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ይቀመጥ የነበረን አንድ ሰው ከዮሐንስ ጋር የነበረው ጴጥሮስ «...ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው። በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና» (ሐዋ 3:1-7)። በኢዮጴ ጣቢታ የተባለችውን ከሞት አስነሣ (ሐዋ 9:36-42)።

የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላቸውን ሲሰሙ ሐዋርያት ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው። እነርሱም በወረዱ ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ (ሐዋ 8:14-17)።

በመጀመሪያዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እስከ ምዕራፍ 11 ድረስ ጴጥሮስ ዋና አገልጋይ እንደነበረ እናነባለን። በቅዱሳን መካከል የመገረዝ ሕግን ስለመጠበቅ ክርክር በተነሣ ጊዜ ለዚህ እልባት ለመስጠት በኢየሩሳሌም በተደረገው ጉባዔ ጴጥሮስ ትልቅ ድርሻ ነበረው (ሐዋ 15)።





ጴጥሮስ ሁለት የአዲስ ኪዳን መልእክቶችን ጽፎአል። ጳውሎስ ጴጥሮስን የቤተ ክርስቲያን አዕማድ መስለው ከሚታዩት አንዱ መሆኑን ገልጾአል (ገላ 2:9)።

ጴጥሮስ በጌታ የተወደደና የተመረጠ ትልቅ ኃላፊነትና አደራ የተሰጠው ሐዋርያ ነው። ስለ መሪነቱ ዋና ነጥቦችን ስንመለከት ደቀ መዝሙር ሆኖ ሲጠራ በነበረው ሁኔታ እንጀምር።

## 1. ጴጥሮስ በጅማሬው በራሱ ማስተዋል የሚደገፍ ሰው ምሳሌ።

ጴጥሮስ ሁኔታዎችን ጠንቅቆ የሚያውቅና ለሚነሱ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ያለው ይመስለው የነበረ ሰው ነው። ለዚህ ሦስት ሁኔታዎችን ብቻ እንመለከት።

ከአሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት የኢየሱስን የልብሱን ጫፍ ዳስሳ የደምዋ ፈሳሽ በቆመ ጊዜ ጌታ «የዳሰሰኝ ማን ነው? አለ። ሁሉም በካዱ ጊዜ፤ ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩት አቤቱ፤ ሕዝቡ ያጨንቁሃልና ያጋፉህማል፤ የዳሰሰኝ ማን ነው ትላለህን? አሉ» (ሉቃ 8:45)። እንዲህ ሲናገሩ ጴጥሮስ ከሌሎች ጋር ሆኖ ጌታን ‹እንዴ ግልጽ እኮ ነው! ሰው በበዛበት ሁኔታ መነካካት አይቀርም› ማለቱ ነው። ይህን በማለቱም ከመለኮት ኃይል የሚወጣበትን መንገድ አለማወቁን አሳየ። እንደ ሰው ብቻ ተናገረ።

እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ መከራ እንደሚቀበል፤ እንደሚሞትና በሦስተኛውም ቀን እንደሚነሣ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገልጥላቸው «ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።» ይህን ሲል ጴጥሮስ እንደ ሰው ለጌታ ያለውን ፍቅር መግለጹ ባልከፋም ነበር ግን ከማን

ጋር እንደሚነጋገር አላስተዋለም:: ስለዚህ ጌታ «...ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው» (ማቴ 16:22-23፤ ማር 8:33)::

ጌታ በተያዘበትም ምሽት ሰይፍ አውጥቶ «የሊቀ ካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠ» (ዮሐ 18:10):: ይህን በማድረጉ ጌታ ጴጥሮስን አላመሰገነውም ነገር ግን «ሰይፍህን ወደ ሰገባው ከተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው» (ዮሐ 18:11):: ይህም ለጴጥሮስ ሌላ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር መተላለፉን ያሳያል:: ሆኖም እንዲህ ዓይነቱን ሰው ነበር ጌታ ኢየሱስ ‹ዓለት› ብሎ የጠራው:: እርሱ ዓለት እንደሚያደርገው ስለሚያውቅ!!

በጴጥሮስ የመጀመሪያ ደቀ መዝሙርነት ዓመታት እነዚህን መሰል በርካታ ሁኔታዎች ነበሩ:: ‹እንደመጣለት› የሚናገር፤ ‹ሙሉና ትክክለኛ መልስ ያለው የሚመስለው የጌታን ሀሳብ ሳይገነዘብ ‹ሰው ብቻ› የሆነ ነበር:: እንዲህ ዓይነት ሰው ወደ መሪነት ለማደግ ነገሮችን ጌታ በሚያይበት ዓይን ማየትና አደራረጉን በጥሞና በማስተዋል ከጌታ መማር አለበት::

አስተዋይ መሪ ስለ መንፈሳዊ ነገር የሚያውቀው ጥቂት ብቻ መሆኑን የሚገነዘብና ሁልጊዜ ከጌታ ለመማር የተዘጋጀ መሆን አለበት::

## 2. ጴጥሮስ ክርስቶስን በመከተል ጀምሮ በመከተል የጨረሰ ደቀ መዝሙር::

ለሦስት ዓመት ያህል ሲከተለው ለቆየው ጴጥሮስ የጌታ ኢየሱስ የመጨረሻ ቃሉ «ተከተለኝ» የሚል ነበር:: ይህን ያለው ወደፊት





መጨረሻው ምን እንደሚመስል ካመለከተው በኋላ ነበር:: ጌታ ስለ ጴጥሮስ መጨረሻ ሲናገር «እውነት እውነት እልሃለሁ፤ አንተ ጕልማሳ ሳለህ ‘ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፤ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው። በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ። ይህንም ብሎ ተከተለኝ አለው» (ዮሐ 21:18-19)።

ጴጥሮስ በኑሮውና በተቀበለው መከራ የክርስቶስን ምሳሌነት ተከትሏል፤ ወንድሞችም የክርስቶስ ተከታይ እንዲሆኑ ይመክራል:: «ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሡ፤ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፤ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና» (1ጴጥ 2:20-21) በማለት ይጽፋል:: ጴጥሮስ ጥሩ የክርስቶስ ተከታይ ነበር::

በተጨማሪም ጴጥሮስ ጥሩ የክርስቶስ ተከታይ በመሆኑ በመልእክቶቹ ሁሉ የጌታውን ምሳሌነት አጉልቶ ይገልጽ ነበር:: ይህንም ለክርስትና ጉዞ ጽናት ምክንያት አድርጎ ሌሎችን ይመክርበታል:: «ክርስቶስም በሥጋ ስለ እኛ መከራን ስለተቀበለ፥ ከእንግዲህ ወዲህ በሥጋ ልትኖሩ በቀረላችሁ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ሰው ምኞት እንዳትኖሩ፤ እናንተ ደግሞ ያን አሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋችሁ ያዙት...» (1ጴጥ 4:1-2) አለ::

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳው ጴጥሮስ የሞተው ስለ ክርስቶስ ሰማዕት ሆኖ በሮም ንጉሥ በኔሮ ዘመን በ64 ዓ.ም. ነው:: በመስቀል ሊሰቅሉት ሲሉ ‹እንደ ጌታየ ባለ መስቀል እኔ ልሰቀል የተገባሁ አይደለሁም› በማለት ተዘቅዝቆ እንዲሰቀል በጠየቀው

መሠረት ራሱ ወደ ታች ተዘቅዝቆ መሰቀሉ ተገልጾአል:: ጴጥሮስ እስከ ፍጻሜ ጌታውን የተከተለ፤ በእምነት የበረታና ሩጫውን የፈጸመ ሰው ነው::

እንግዲህ የመሪ ጥሪና ኃላፊነት ለእድሜ ዘመኑ ሁሉ የክርስቶስ ተከታይ መሆን ነው:: ጌታ ጴጥሮስን በመጀመሪያ ሲጠራው ‹ተከተለኝ› ብሎ እንዲሁም ከምድር ሊለይ ሲቃረብ በድጋሚ ‹ተከተለኝ› እንዳለው ለሁሉም ደቀ መዝሙር መምህሩ ኢየሱስ ዛሬም የሚናገረው ‹ተከተለኝ› ብሎ ነው:: ጥሩ መሪ የክርስቶስ ጥሩ ተከታይ ነው:: ጥሩ የሚከተል ጥሩ ይመራል::

## 3. ጴጥሮስ የተቀበለውን አደራ የፈጸመ እረኛ::

መልካሙ እረኛ ጌታ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት ለጴጥሮስ የእረኝነት አገልግሎት እንደ ሰጠው በዮሐ 21፡15-17 እንመለከታለን::

> «ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ግልገሎቼን አሰማራ አለው። ደግሞ ሁለተኛ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው። ሦስተኛ ጊዜ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ ትወደኛለህን? አለው። ሦስተኛ ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና። ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ኢየሱስም በጎቼን አሰማራ...» አለው።

ይህን ክፍል በመውሰድ ከበጎች ባለቤትነት ጋር በተያያዘ የተደረገውን ገለጻ በዚሁ መጽሐፍ በቅጽ ፬ ተመልክቷል:: አሁን እዚህ ባጭሩ የምንመለከተው የእረኝነት አደራን ከመፈጸም ጋር በተያያዘ ነው::





ጴጥሮስ የተሰጠውን የእረኝነት አገልግሎት አደራውን ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ እንደተወጣ ከሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያው ምዕራፍ ጀምሮ ይታያል:: በተለይ ደግሞ እርሱ በጻፋቸው መልእክቶች በግልጽ ይነበባል::

በ1ጴጥ 5፡2-4 ባለው ክፍል «በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ:: የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ» እያለ ሽማግሌዎችን ይመክራል:: በዚህ ምክሩ ጴጥሮስ ለሽማግሌዎች፡-

- መንጋው የእግዚአብሔር መሆኑን እንዲገነዘቡ፤
- በመግዛት ሳይሆን በማገልገል እንዲጠብቁ፤
- ከመንጋው ባለመራቅ እየጎበኙ እንዲጠብቁ፤
- ራስን ለማገልገል ሳይሆን በሙሉ ፈቃደኝነት እንዲጠብቁ፤
- እነርሱም በአለቃ ሥር የሚያገለግሉ እረኞች መሆናቸውን በማወቅ እንዲያገለግሉ፤

ያስገነዝባቸዋል:: ይህ ጌታ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ከሰጠው የእረኝነት አደራ ጋር ይመሳሰላል:: ስለዚህ ጴጥሮስ ጥሩ ተማሪና የተሰጠውን አደራ በታማኝነት የፈጸመ ሰው ነበር ማለት ነው:: ጴጥሮስ የመልካም እረኝነት ትርጉም የገባው ሐዋርያ ነበር::

ጴጥሮስ ሽማግሌ ነበር፤ በጌታም ሐዋርያ ተብሎ ተጠርቷል:: እንዲህ የተለያየ የአገልግሎት ማዕረግ ቢኖረውም አገልግሎቱ ከሰዎች (ከበጎች) ጋር የተገናኘ በመሆኑ አፈጻጸሙ በመጠበቅ (በእረኝነት) ነው:: እንዲሁም ክርስቲያን መሪዎች ከሰዎች ጋር

በሚኖራቸው ግንኙነት የእረኝነትን አገልግሎት መፈጸም ይጠበቅባቸዋል::

## 4. ጴጥሮስ አገልጋይነትንና ትሕትናን የተማረ ሐዋርያ::

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን መምህር ወይም አለቃ የሆነ ሰው ተከታዮቹን እንደሚያገለግል አይታሰብም ነበር:: ጌታም ሲያስተምር «...የአሕዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን» (ማቴ 20:25-27) ብሏል::

ጌታ ኢየሱስ ማበሻውን ታጥቆ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብ ሲጀምር ጴጥሮስ «ጌታ ሆይ፤ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ አለው። ጴጥሮስም የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው» (ዮሐ 13:6-10)። ጴጥሮስ ጌታን የእኔን እግር አታጥብም ማለቱ ‹መሪ ከሚያገለግላቸው በላይ ስለሆነ እግር ማጠብ የለበትም› የሚለውን አመለካከት መያዙን ይጠቁማል:: ደግሞም እንደ ደቀ መዝሙር ለጌታውና ለመምህሩ ያለውን አክብሮት መግለጡ ነበር:: ይሁን እንጂ ጌታ ኢየሱስ እያደረገ የነበረው እንደ ሰው ልማድ የሆነ ነገር አልነበረም:: ትምህርቱ እጅግ ጥልቅ ነው::

በኋላ ላይ ጴጥሮስ ይህን ትምህርት እንደተማረ መገንዘብ ይቻላል:: ቆርኔሌዎስ ከእግሩ በታች ወድቆ ሲሰግድት «ጴጥሮስ ግን ተነሣ፤ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው» (ሐዋ 10:26)። እንዲሁም ሐዋርያ የትንሣኤው ምስክር ሆኖ ሳለ ራሱን ከሌሎች





ጋር አመሳስሎ «ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ ...የሆንሁ» (1ጴጥ 5:1) በማለት ይናገራል::

አገልግሎትንም በተመለከተ ራስን ዝቅ በማድረግ መሆኑን ሲገልጽ «እርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባሪያዎች ሁኑ...» (1ጴጥ 2:16)፤ «እርስ በርሳችሁ አገልግሉ» (1ጴ 4:10) ይላል:: እንዲሁም «...ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ» (1ጴጥ 5:5) ሲል ጌታ ኢየሱስ የማበሻውን ጨርቅ ታጥቆ ማገልገሉንና ጴጥሮስም ያንን እንደሚያስታውስ መገመት ቀላል ነው:: ስለዚህ አገልጋይ ማለት በትሕትና የሚያገለግል የእግዚአብሔር ባሪያ መሆኑን ጴጥሮስ ተማረ::

እንዲሁም ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር ባሪያዎች መሆናቸውን ተገንዝበውና የጌታ ኢየሱስን ምሳሌ በመከተል ከልማድና ከባሕል በላይ በሆነ ሁኔታ በትሕትና ማገልገል ይጠበቅባቸዋል::

## 5. ጴጥሮስ ከውድቀት በንስሐ የሚመለስ መሪ ምሳሌ

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ጴጥሮስ በሕይወቱ ብዙ ጊዜ ተንሸራቷል:: ይህ ድካሙ ነው ማለት ይቻላል:: ይሁን እንጂ ጴጥሮስ ለዲያብሎስ የማይመች፤ ፈጥኖ ከውድቀት የሚመለስ የብርቱ መሪም ምሳሌ ነው:: ይህን ለማስረዳት ጥቂት ሁኔታዎችን እንመለከት::

ሌሊቱን ሙሉ ዓሣ ለማጥመድ ሞክረው ስላልሆነላቸው መረቦቻቸውን ሲያጥቡ ከነበሩት ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን «ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ» ባለው ጊዜ ሊከራከር ጀምሮ ነበር:: ግን መለስ ብሎ «በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ» አለ:: ከዚያም እጅግ ብዙ ዓሣ እንደያዙ ሲመለከት

«...በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወድቆ ጌታ ሆይ፤ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ አለው» (ሉቃ 5፡4-8)።

ጴጥሮስ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» (ማቴ 16፡16) ባለና «ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም ...ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን፥ ከቶ አልክድህም» (ማቴ 26፡32-35) ብሎ በተናገረ በጥቂት ቀናትና ወራት ልዩነት «የምትዪውን አላውቀውም ...ሰውየውን አላውቀውም ...ሰውየውን አላውቀውም» (ማቴ 26፡69-74) ብሎ ሦስት ጊዜ የካደ ሰው ነው:: መቼም ይህ ትልቅ ክህደት ነው:: ግን ደግሞ በዚያች ሌሊት ‹ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የኢየሱስ ቃል ትዝ› ሲለው «መራራ ልቅሶ አለቀሰ» (ማቴ 26፡75፤ ሉቃ 22፡62)::

ጴጥሮስ የጌታ ደቀ መዝሙር ከነበረው ከአስቆሮቱ ይሁዳ ጋር ሲተያይ ትልቅ ልዩነት አለው:: ጌታን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ «እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ፥ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሎች መልሶ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ። ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ» (ማቴ 27፡3-5)። ይሁዳ የፈጸመው ድርጊት ስህተት መሆኑን ቢያውቅም ወደ እግዚአብሔር የሚመለከት የንስሐ ልብ ግን አልነበረውም:: ጉዳዩን የሸያጭና የግዥ፤ የገንዘብ ጉዳይ ብቻ ስላደረገው ገንዘቡን ለመመለስ ፈለገ:: ጴጥሮስ ግን በክህደቱና በድካሙ ውስጥ አልቆየም፤ በንስሐ ተመለሰ::

መሪዎች ሰዎች ናቸው፤ ኃጢአት የማያደርጉ አይደሉም:: «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን





አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» (1ዮሐ 1፡8-10):: ይሁን እንጂ ‹ወደፊት መውደቃቸው አይቀርም› በሚል አንጠባበቅም::

ነገር ግን ምናልባት በአንድም በሌላም ሁኔታ ችግር ከገጠማቸው ውድቀታቸውን አጥብቆ ለሚመኘው ጠላት:-

> «እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እመለከታለሁ፤ የመድኃኒቴንም አምላክ ተስፋ አደርጋለሁ፤ አምላኬም ይሰማኛል። ጠላቴ ሆይ፤ ብወድቅ እነሣለሁና፤ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቻለሁና እስኪምዋገትልኝ ድረስ፤ ፍርድን ለእኔ እስኪያደርግ ድረስ ቍጣውን እታገሣለሁ። ወደ ብርሃን ያወጣኛል፤ ጽድቅንም አያለሁ። ጠላቴም ታያለች፤ እኔንም አምላክህ እግዚአብሔር ወዴት ነው? ያለች በእፍረት ትከደናለች» (ሚክ 7፡7-10)::

የሚሉ ሊሆኑ ይገባል:: ስለዚህ ፈጥነው በንስሐ ወደ ጸጋው ዙፋን በመቅረብና ምሕረትን ከሰጪው ከእግዚአብሔር በመለመን ሊመለሱ ይገባል:: ከዚያም ይቅር ስለተባለላቸው ስለቀደመው ውድቀታቸው ሳያስቡ በእግዚአብሔር ጸጋ ታምነው የሚቀጥሉና ወደፊት የሚገሰግሱ ናቸው:: እግዚአብሔር መሐሪ ነው::

## 6. ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ታላቅ ለውጥ የታየበት ደቀ መዝሙር::

ጴጥሮስ ፈሪ የሚባል ሰው እንደ ነበር ተመልክተናል:: ከጌታ ትንሣኤና ከባለ ኀምሳ ቀን በኋላ ይህ ባሕርዩ በእጅጉ ተለውጧል::

ጌታ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ከሚጠባበቁትና በጸሎት ከበረቱት መቶ ሀያዎቹ መካከል ነበር:: ጌታ ለሰጣቸው አገልግሎትም ‹የውስጥ አደረጃጀቱን› ለማሟላት

ይሁዳ በተዋት ቦታ የሰውን ልብ የሚያውቅ እግዚአብሔር ሐዋርያ እንዲሾም በወንድሞች መካከል መሪ ሆኖ አደራጅቷል፡፡

መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ (ሐዋ 2፡1-4) ደግሞ በጴጥሮስ ሕይወት ታላቅ ለውጥ ታየ፡፡ በባለ ኀምሳ ቀን ከአሥራ ሁለቱ ጋር ቆሞ በኢየሩሳሌም ለተሰበሰቡት ወንጌል ሰበከ፡፡ ከሁለት ወር ያህል በፊት ጴጥሮስ በዚያው ከተማ ጌታን ‹አላውቀውም› ብሎ ነበር፡፡ አሁን ግን «...እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን» (ሐዋ 2፡32) በማለት በሕዝብ ፊት ይናገራል፡፡ ይህን ያህል ድፍረት ጴጥሮስ ከየት አመጣው? መልሱ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መልበሱ ነው፡፡ አዎ ከባለ ኀምሳ ቀን በኋላ ጴጥሮስ በእጅጉ ደፋር ሰው ሆኗል፡፡

አንድ ጊዜ ይፈራቸው የነበሩትን «እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች፤ ...እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደኅና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፤ ለእናንተ ለሁላችሁ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን። እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፤ የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው» (ሐዋ 4፡8-11) ሲል አነጋገሩ ኢየሱስን እንደሚያውቀው መግለጽ ብቻ ሳይሆን እነርሱ በኢየሱስ ላይ ያደረጉት ሁሉ ስህተት መሆኑን በማስረዳትና በመውቀስ ጭምር ነበር፡፡ ይህም ትልቅ ድፍረት ነው፡፡

እንዲሁም ጴጥሮስና ዮሐንስን «በኢየሱስ ስም ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ...» ባዘዙአቸው ጊዜ «እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ሆነ ቍረጡ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው» (ሐዋ 4፡18-20)፡፡ ይህንን ማለቱ ምን እንደሚያስከትልበትም ያውቃል፡፡ ያም ቢሆን በድፍረቱ ቀጠለ፡፡ ከዚያም በኋላ «...ገረፉአቸው፥ በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው። እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ





የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤ ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር» (ሐዋ 5፡40-42) ተብሎ ተጽፎአል።

ደፋሩ ጴጥሮስ በአገልግሎቱ የኢየሱስን ስም ከፍ ከፍ አድርጎ ይናገር ነበር፡፡ ድውዩን «ያለኝን እሰጥሃለሁ በኢየሱስ ስም ተነሳና ተመላለስ» (ሐዋ 3፡6) አለው፡፡ እንዴት እንደተፈወሰ ሲናገርም «በናዝሬቱ በጌታ በኢየሱስ ስም ደህና ሆነ» (3፡16፤ 4፡10) አለ፡፡ እንዲሁም «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (4፡12) ብሎ አወጀ። ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ ደስተኞች ነበሩ (5፡41)፡፡ ተቃዋሚዎች የኢየሱስ ስም እንዲጠራና እንዲታሰብ ስለማይፈልጉ በዚህ ስም እንዳናገሩ አዘዟቸው (4፡17፤18፤ 5፡28፤40)፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ደፋር ሆኖ የተለወጠው ጴጥሮስ በመልእክቱ «ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር» (1ጴጥ 4፡16) በማለት ቅዱሳንን ይመክራል።

ፈሪ የነበረው ጴጥሮስ ከባለ ኀምሳ ቀን በኋላ ደፋርና ታማኝ ሐዋርያ ሆነ፡፡ በጴጥሮስ ሕይወት እንደታየው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአገልጋይ ሕይወት ታላቅ ኃይልና ድፍረትን ይሰጣል፡፡ «እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን» (5፡32) እንዳሉ የኢየሱስ ምስክር ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን በውል መገንዘብ ይገባቸዋል፡፡

## 7. ጴጥሮስ ሰው ሁሉ በክርስቶስ እኩል መሆኑን የተገነዘበ ተማሪ::

በብሉይ ኪዳን ሕዝብ አይሁዳዊና፣ አሕዛብ ወይም የተገረዘና ያልተገረዘ በሚል በሁለት ዋና ክፍል ይከፈል ነበር:: የተገረዙ የሚባሉት የአብርሃምን ኪዳን የተቀበሉ (ዘፍ 17፡9-13) ናቸው:: ጴጥሮስ ዕብራዊ ስለሆነ ከአብርሃም ዘር ነው:: ለዚህ ነበር «አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ» (ሐዋ 10፡28) በማለት የተናገረው::

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍ፡-

> «አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፤ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው» (ኤፌ 2፡13-16)::

ብሏል:: ጳውሎስ ሰው ሁሉ በክርስቶስ በእምነት እኩል መሆኑን አጠንክሮ አስተምሯል:: አይሁድ ላልሆኑት የገላትያ ክርስቲያኖች፡-

> «በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና። እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ» (ገላ 3፡26-29)





ይላቸዋል:: ይህን እውነት ጴጥሮስ በጥልቀት ያልተረዳው ይመስላል:: ስለሆነም ከአሕዛብ ጋር አብሮ ላለመብላት «ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ያፈገፍግ ነበር::» ጳውሎስ ይህን ሁኔታ ግብዝነት ይለዋል:: «የቀሩትም አይሁድ ደግሞ፤ በርናባስ ስንኳ በግብዝነታቸው እስከ ተሳበ ድረስ፤ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ» (ገላ2፡11-13) ይላል:: ይህ በመጀመሪያው ዘመን በነበሩ ክርስቲያኖች መካከል አለመግባባትን የፈጠረ ጉዳይ በመሆኑ በኢየሩሳሌም የተደረገው የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ አንዱ ውሳኔ አይሁድን እንዲመስሉ «...ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን እንዳናስቸግራቸው» (ሐዋ 15፡9) የሚል ነበር ::

እዚህ ላይ ከጳውሎስ ድርጊት የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር አለ:: ጴጥሮስና ጳውሎስ ሁለቱም ሐዋርያት ናቸው:: እንዲያውም ጴጥሮስ ሐዋርያ በመባል ጳውሎስን ይቀድማል:: በሌላም ጊዜ ‹ዐምድ› በማለቱ ጳውሎስ ለጴጥሮስ ያለውን አክብሮት ይገልጻል:: ሆኖም በቅዱሳን መካከል የሚኖረው ‹መከባበር› በእውነት ላይ የተመሠረተ፤ በጽድቅና በቅንነት መሆን አለበት::

መሪዎች ለሰው ፊት ባለማድላትና ግብዝነት የሌለው ኑሮ በመኖር ምሳሌዎች መሆን ይገባቸዋል:: ወንጌል ፊር ለቆ ሲሄድ እያየ ሌላው ሰው እንዳይቀየም ወይም ከፍ ባለ የአገልግሎት ሥልጣን ካለ ሰው ጋር ላለመቃቃር በሚል እውነትን መሸቃቀጥ የእውነተኛ ክርስትና መልክ አይደለም:: ክርስትን ፍቅርን በእውነት መናገር እንጂ ዲፕሎማሲም አይደለም:: ስለዚህ መጽሐፍ «ብረት ብረትን ይስለዋል፤ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል» (ምሳ 27፡17) እንደሚል አንዱ ሲስት ሌላው ሊያቀናው ከእውነት የተንሸራተትን መምከርና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ መገሰጽ ይገባል:: ይህ የሚደረገው ለቤተ ክርስቲያን ጤንነት፤ ለወንጌል ጉልበትና ለእግዚአብሔር ክብር ነው::

እንዲሁም ጴጥሮስ በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ በመልእክቱ ስለ ጳውሎስ የሚሰጠው ምስክርነት ምን ያህል ገር ሰው እንደሆነ ያመለክታል:: «የጌታችንም ትዕግሥት መዳናችሁ እንደ ሆነ ቍጠሩ። እንዲህም የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፤...» (2ጴጥ 3:15) በማለት ጳውሎስ የተወደደ ወንድም መሆኑን በመግለጽና የተሰጠውን ጸጋ በማክበር ጻፈ:: ጴጥሮስ በጌታ ወንድሙ ከሆነው ከጳውሎስ ተግሳጽን ተቀብሎአል፤ ይሁን እንጂ በጌታ ያለው ወንድምነት የጸና ነው፤ በሰው ላይ ያለውንም ጸጋ ያከብራል::

## 8. ጴጥሮስ ጌታ እንዳዘዘው ወንድሞቹን ያጸና ታዛዥ::

ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን «እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» (ሉቃ 22:32) በማለት አዞት ነበር:: ይህን አገልግሎት ጌታ ወደ ሰማይ ካረገበት ጊዜ ጀምሮ በደቀ መዛሙርት መካከል እንደ ጀመረ እንገነዘባለን:: በተለይ ደግሞ ይህን የጌታ ትዕዛዝ በአገልግሎቱ እንደ ፈጸመ ጥቂቱን እንመለከት::

በመልእክቶቹ ቅዱሳንን የሚመክረው በክርስቶስ ያገኙትን ተስፋ እየጠበቁ በመከራ እንዲጸኑ፤ የክርስቶስን ምሳሌ እንዲከተሉ፤ የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ በመሆን እንዲያድጉና (2ጴጥ 1:5-7) የጌታን ቀን በመጠባበቅ፤ እግዚአብሔርን በመምሰል ያለነቀፋና ያለነውር እንዲኖሩ (2ጴጥ 1:4፤ 3:14) ነው:: ይህ ወንድሞችን የማበርታት አገልግሎት ነው::

ክርስቲያኖች በዚህ ምድር መጻተኞች ስለሆኑ ኑሮአቸው የእንግድነት ዘመን ነው፤ የዘላለም ቤታቸው በሰማይ ነው:: የማይጠፋና የማያድፍ ተስፋ ዳግመኛ ለተወለዱት ሁሉ በሰማይ ቀርቶላቸዋል:: የቀደሙት መከራ እንደተቀበሉ ለክርስቲያን መከራ





መቀበል የእግዚአብሔር ሀሳብ ነው:: መከራ ለሚቀበሉ ክርስቶስ ምሳሌያቸውና ተስፋቸው ነው:: ስለዚህ ቅዱሳን በመከራ ውስጥ ቢያልፉም በጣም እንዳይደነቁ፤ ይልቁን ክብር እንደሚጠብቃቸው እንዲያውቁ፤ በክርስቶስ መገለጥ ላይ ተስፋ እንዲያደርጉና በሚደርስባቸው መከራ ሁሉ እጅግ ደስ እንዲላቸው ይመክራቸዋል (1ጴጥ 1:3-12):: «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ፤ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይስጡ» (1ጴጥ 4:19) በማለት ያሳስባል። በመከራ ጊዜ ለሁሉም ሁኔታ የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ ነው::

እንዲሁም የተቀደሰ ሕዝብ ስለሆኑ በቅድስና እንዲኖሩ፤ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ (1:22-25)፤ ለመንፈሳዊ እድገት የሚረዳቸውን ንጹሑን የቃል ወተት እንዲመኙ (2:1-3)፤ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ለማቅረብ ስለተጠሩ ሕያው ድንጋይ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ እየቀረቡና ሕያዋን ድንጋዮች እየሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን እንዲሰሩ (2:4-10)፤ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንዲርቁ (2:11) በአጽንዖት ይመክራቸዋል:: የክብር እምነት ያገኙ ስለሆኑና የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ እንዲሆኑ ስለተመረጡ እግዚአብሔር የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን እንደሰጣቸው እንዲገነዘቡ ያስረዳቸዋል (2ጴጥ 1:3-11):: ይህን የሚጽፍላቸውም በሕይወት እስካለ ድረስ (ከመሞቱ በፊት) ‹ሊያነቃቸው› (1:13) ነው::

ጴጥሮስ ከኢየሱስ መማለድ የተነሣ የሰይጣንን ማበጠር አምልጦ የጌታ ተከታይ ሆኖ የኖረ ሰው ነው:: እስከ መጨረሻውም በመጽናት «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን አውቃለሁና» (2ጴጥ 1:14) በማለት ሩጫውን የጨረሰ ታማኝ ሐዋርያ ነው:: ከመሞቱ በፊትም የታዘዘውን በትጋት ፈጸመ::

በሐዋርው ጴጥሮስ አገልግሎት እንደተመለከትነው ወንድሞችን የሚያጸና መሪ ትኩረቱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማሳሰብ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ባሕርይ ተካፋዮች እንዲሆኑና በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እንዲያድጉ ማበረታት ነው፡፡ ጴጥሮስ ይህን አድርጎአል፡፡

## 9. ጴጥሮስ በእግዚአብሔር እውቀትና ጸጋ ያደገ ደካማ ሰው፡፡

በሕይወቱ ብዙ የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛለት ጴጥሮስ «በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ...» (2ጴጥ 3፡18) በማለት ሌሎችን ይመክራል። ስለ ክርስቶስ በማወቅና በጸጋ ያደገ ሰው ነው፡፡

በታንኳዋ ውስጥ አስራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ቢኖሩም ወደ ጌታ ለመሄድ የፈለገና የጠየቀ ጴጥሮስ ብቻ ነበር፡፡ በዚህ ድርጊቱ እምነት ያነሰው ሰው መሆኑ ተገለጠበት፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለው እምነት ማደግ ነበረበት፡፡ ከስህተቱ እየተማረ በሕይወቱ ያድግ ነበር፡፡ ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስን ‹ይህ አይሁንብህ› ሲለው ለጌታው የነበረውን መውደድ ቢያመለክትም መውደድ ከእግዚአብሔር እውነት ጋር መሄድ አለበት፡፡ ጌታ የገሰጸውም በእግዚአብሔር ሀሳብ እውቀት ባለማደጉና የሰው የሆነውን ብቻ በማሰቡ ነበር፡፡ እኛ የምናደረገውን በመልካም ምኞት ብናደርገውም የእግዚአብሔርን ሀሳብ በመረዳት ካላደረግነው ‹አንተ ለእኔ እንቅፋት ነህ...› የሚለውን የጌታ ተግሳጽ ልንሰማ እንችላለን፡፡

ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሲያጥብ ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ ለማስተማር አልነበረም፡፡ ትምህርቱ ለእርስ በርሳቸው ትሑታን እንዲሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ‹እግሩን የታጠበ› ሲል እግራችን በቀና





መንገድ ከተራመደ እጃችን፤ ራሳችንና ሌላው ሰውነታችን ሁሉ አብሮ ይጓዛል፤ ጌታ በሚፈልግብን ጎዳና ይሄዳል በሚል ሲያስረዳው ነው፡፡ ጴጥሮስ በጊዜው ይህ አልገባውም፡፡ ግን በክርስቶስ እውቀት ሲያድግ ‹ተቀደሱ›፤ ‹ትሕትናን እንደ ልብስ ልበሱ› በማለት ሌሎችን ያስተምር ነበር፡፡

ጌታን ‹አላውቀውም› ብሎ በተደጋጋሚ የካደ ሰው ለትንሣኤው ምስክር ለመሆንና እንዲህ ዓይነቱን ታላቅ በረከት ለማየት የመጀመሪያው መሆን ባልተገባም ነበር፡፡ ግን የእግዚአብሔር ርኅራኄ አስደናቂ ነው፡፡ አሠራሩም ከሰው ሀሳብ የላቀ ነው፡፡ ከትንሣኤውም በኋላ ጴጥሮስን ሲያገኘው ስለካደው አልገሰጸውም ይልቁን ወደ እርሱ ታንኳ ሄዶ ምሳ አብሮ በላ፡፡ ‹ከዚያም ትወደኛለህን?› ብሎ በተደጋጋሚ ጠየቀው፤ የአገልግሎት አደራም ሰጠው፡፡

ጴጥሮስ እስከ ምድር ዳርቻ እንዲሄዱ ጌታ የሰጠውን ታላቁን ተልእኮ (ማቴ 28፡18-20፤ ሐዋ 1፡8) ከተቀበሉት መካከል ቢሆንም ከአሕዛብ ጋር የመቀላለቀል ችግር ነበረበት፡፡ ሆኖም ጴጥሮስ ስለ ርኩስ ምግብ ራእይ ካየ በኋላ (ሐዋ 10፡9-16) እግዚአብሔር አስተማረው አሕዛብን ጨምሮ ርኩስ የሆነ ሰው አለመኖሩን (ሐዋ 10፡34-48) ተገነዘበ፡፡ ከማንኛውም ወገን ቢሆን እግዚአብሔርን የሚፈራና በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን የሚያደርግ ተቀባይነት እንዳላቸው በመገንዘብ በክርስቶስ እውቀት አደገ፡፡

ጌታ ጴጥሮስን ወዳሰበለት ደረጃ ለማድረስ በብዙ ትዕግስትና ፍቅር ተሸክሞታል፤ መርቶታል፤ ጸጋውን አብዝቶለታል፡፡ ጌታ ‹ሰው አጥማጅ አደርግሃለሁ› ያለውን ለጥሪው ብቁ አደረገው፡፡ እንደ ንስር በክንፎቹ ተሸክሞ ዳር አደረሰው፡፡

ጌታ ሰዎችን ከሸሽታቸው የሚመልሰበት፤ ከፍርሃታቸው ነጻ የሚያወጣበት መንገድ አስደናቂ ነው:: መቼም በአንድ ጊዜ የተዋጣለት መሪ ሆኖ የሚያድግ ሰው አይኖርም:: ሰው ስለሆነ ከውድቀቱ እየተማረ፤ በክርስቶስ እውቀት እያደገና በእግዚአብሔር ጸጋ እየበረታ የሚሄድ ሰው ዳር ይደርሳል:: እግዚአብሔር ሰውን ለአገልግሎት ሲጠራ በሚጠራው ሰው ችሎታና ጥንካሬ ላይ ተማምኖ እንዳልሆነ የጴጥሮስ ሕይወት ይነግረናል:: የመሪ ብቃቱ እግዚአብሔር ነው::

10. ‹ታላቅ› የሚባለው ሐዋርያም እንደ እኛ ሰው ነው::

ጴጥሮስን ስናነሣ ጌታ ኢየሱስ እንዴት ለደቀ መዝሙርነት መረጠው?፤ እንዴት ከሦስቱ መካከል አንዱ አደረገው? እንዴት ዓለት አለው? እንዴትስ ከትንሣኤው በኋላ ለካደው ከሁሉ ቀድሞ ታዬ? የሚሉና ተመሳሳይ ጥያቄዎች ይነሳሉ:: ሰው ይህን የሚጠየቀው ጴጥሮስ የውስጥ ብርታት ያለው ስለማይመስል ነው:: አንዳንዴም ለቦታው የማይመጥን አድርገን እናስበዋለን:: ገፋ ሲልም የጴጥሮስ ዓይነት ሰው አሁን ባለንበት ዘመን ለመሪነት ቢታሰብ ‹ብቁ› ስላይደለ አንቀበለውም ብለን የምናስብም አንታጣም:: ለዚህ ሁሉ ጥያቄ መልሱ ያለው ከጴጥሮስ ሳይሆን ‹ተከተለኝ› ብሎ በመረጠው ማንነት ላይ ነው:: ጴጥሮስማ እንደ እኛ ሰው ነበረ!!







ጴጥሮስ እንደ እኛ ሰው ለመሆኑ ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ እንውሰድ::

አንድ ሌሊት ደቀ መዛሙርቱ በታንኳ ሲሄዱ ጌታ ኢየሱስ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሲመጣ ምትሐት መስሏቸው ፈሩ:: ጴጥሮስም ጌታን ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ ባለው ጊዜ ና አለው። ጴጥሮስ «...ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ኢየሱስ ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ። ነገር ግን የነፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ፤ ሊሰጥምም በጀመረ ጊዜ፤ ጌታ ሆይ፤ አድነኝ ብሎ ጮኸ። ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና አንተ እምነት የጎደለህ፤ ስለምን ተጠራጠርህ? አለው» (ማቴ 14:28-31):: ጴጥሮስ እምነት የጎደለውና ተጠራጣሪ ሰው ነበር::

እንዲሁም አይሁድን ይፈራ ነበር:: ስለፈጸመው አንድ ስህተት ጳውሎስ እንደሚከተለው ጽፎአል::

> «ነገር ግን ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት፥ ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና። አንዳንድ ከያዕቆብ ዘንድ ሳይመጡ ከአሕዛብ ጋር አብሮ ይበላ ነበርና፤ በመጡ ጊዜ ግን ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ያፈገፍግ ነበርና ከእነርሱ ተለየ። የቀሩትም አይሁድ ደግሞ፥ በርናባስ ስንኳ በግብዝነታቸው እስከ ተሳበ ድረስ፥ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ። ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር፤ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው? አልሁት» (ገላ 2:11-14)።

ጴጥሮስ ሰውን የሚፈራ እንደ እኛ ሰው ነበር::

ጴጥሮስ ጌታን ‹አይሁንብህ› ሲለው ጌታ ግን «...ወደ ኋላዬ ሂድ፤ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና» (ማር 8:33) ብሎታል:: ጴጥሮስ ለጌታ የሰጠው መልስ የመውደድና የሀዘኔታ ቢመስልም የእግዚአብሔርን የዘላለም ሀሳብ



ያልተረዳ ሰው ነበር። እንዲሁም ኤልያስና ሙሴም ታይተው ከኢየሱስ ጋር ይነጋገሩ በነበረበት ጊዜ ‹ሦስት ዳሶች እንሥራ› ማለቱን መጽሐፍ ቅዱስ ከፍርሃት የተነሳ «የሚለውን አያውቅም ነበር» (ማር 9፡4-6) ብሎታል። በተጨማሪም በጌቴሴማኒ ጌታ «ስምዖን ሆይ፤ ተኝተሃልን? አንዲት ሰዓት ስንኳ ልትተጋ አልቻልህምን?» (ማር 14፡37) እንዳለው እንደ እኛ ሰው የሆነው ጴጥሮስ ያን በመሰለ የጭንቅ ሰዓት እንኳ ቢሆን ስንፍናና አለመትጋት ታይቶበታል።

በአጠቃላይ ኬፋ የጌታ ደቀ መዝሙር ነው፤ ጌታ ሐዋርያት ብሎ ከጠራቸው የመጀመሪያው ነው። ከሌሎች ይልቅ ጌታ ወደ ራሱ ካቀረባቸው ደቀ መዛሙርት መካከል ነበር። ዓሣ አጥምዶ ለቀረጥ የሚሆን ገንዘብ ከአፉ እንዲያወጣ እንዳዘዘው (ማቴ 17፡27) ሁሉ ጌታ በተደጋጋሚ የላከው ደቀ መዝሙር ነበር። እንዲሁም «የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤» (ማቴ 16፡19) የተባለ፤ «ከገናናው ክብር፤ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» (2ጴጥ 1፡17) የሚለውን ድምጽ የሰማ ምስክር ነው፤ የትንሣኤውም ምስክር ነው። በአንድ ቀን ሦስት ሺህ እስኪድኑ ድረስ ያደረገ ታላቅ የወንጌል ሰባኪ ነው።

በእጁ ታላላቅ ተአምራት ተደርገዋል። ሽባ ተፈውሷል፤ የሞተም ተነስቷል፤ የጌታን መንፈስ በተፈታተኑት ሐናንያና ሰጲራ ላይ አስደንጋጭ ፍርድ ሰጥቷል (ሐዋ 5፡1-11)፤ በጥላው ሰዎች ይፈወሱ ነበር (ሐዋ 5፡15-16)፤ ከሌሎች ሐዋርያት ጋር በታሰረም ጊዜ መልአክ ከእስር ካወጣቸው ጋር የነበረ ብርቱ ክርስቲያን ነው (ሐዋ 5፡17-21)። ስለ ጌታ ብዙ ዋጋ ከፍሏል፤ ታስሯል፤ ተገርፏል። ሆኖም ግን ኬፋ ከእግዚአብሔር ማስቻል በስተቀር ድካም ያለበት ሰው ነበር።





ጴጥሮስ የችኩልነት፤ የተናገረውን ቃል አለመጠበቅ፤ የክህደት፤ ጌታን ለመገሰጽ የመሞከር አለማስተዋል፤ ፍርሃት፤ ስንፍና፤ የእግዚአብሔርን የዘላለም ሀሳብ አለመረዳት፤ እምነት ማጣትና የመሳሰሉ ድክመቶች ታይተውበታል። እነዚህ ድክመቶች በሁሉም ሰው ዘንድ የሚገኙ የሰውን ደካማነት መግለጫዎች ናቸው። ስለዚህ ጴጥሮስም ጌታ ኢየሱስ በተለወጠበት ጊዜ እንደታዩት ኤልያስና ሙሴ ሁሉ ‹ሰው› ነበረ። ሙሴ በጣም ጠንካራ የሕዝብ መሪ ቢሆንም ‹እንደ እኛ ሰው› መሆኑን በዚሁ ቅጽ ምዕራፍ 2 ተመልክተናል። ኤልያስም ታላቅ የእግዚአብሔር ነቢይ ቢሆንም ‹እንደ እኛ ሰው ነበረ› ብሎ ሐዋርያው ያዕቆብ ጽፏል (ያዕ 5፡17)።

ሙሴ እንዲህ ሕዝብን ነጻ የሚወጣ ታላቅ መሪ፤ ኤልያስ ከሰማይ እሳት እንዲወርድ የሚያደርግ ነቢይ፤ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልቶ በአስደናቂ ስብከቱ በአንድ ቀን 3000 ሰዎች በኢየሱስ እንዲያምኑ ያደረገ ሐዋርያ ቢሆኑም ሁሉም ሰዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ «ሁሉን ያዘጋጀ ግን እግዚአብሔር ነው» (ዕብ 3፡4) እንደሚል በእነርሱ በኩል የተፈጸመው ድንቅ ሥራ ሁሉ ከራሳቸው እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል በደካሞች ሕይወት የሠራው የራሱ ድንቅ ሥራ ነው።

እንደ እኛ ሰው ሆኖ ነገር ግን ድካም የሌለበት ሊቀ ካህናችን የሆነው ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ልብ ማለት ይጠቅማል። እርሱ ስለ እኛ ድካም የሚማልድ፤ አብሮን የሚሰማራ፤ ኃይልን የሚያለብሰን፤ በመልካም እረኝነቱ የሚጠብቀንና የሚመራን ነው። ጴጥሮስን ያስቻለው የእግዚአብሔር ታላቅ ጸጋ ነው። መልካም ክርስቲናዊ መሪ በራሱ ‹ማንነት› የማይታመንና በተሰጠው ጸጋ የማይታበይ ነገር ግን እግዚአብሔርን ብቃቱ ያደረገ ትሑት ሰው ነው።

በአጠቃላይ ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበበት ምሽት ጴጥሮስን «...እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፤ በኋላ ግን

ታስተውለዋለህ» (ዮሐ 13፡7) እንዳለው ደቀ መዛሙርት ብዙ ያልተገነዘቡት ነገር ነበር። ጴጥሮስም ብዙ መንፈሳዊ እውነቶችን እያስተዋለ የሄደው ቀስ በቀስ ነው። አዎ! በዚህ ምድር እስካለን ድረስ ሙሉ መረዳት የለንም፤ በድንግዝግዝ እናያለን።

የጴጥሮስን ሕይወት ልብ ብሎ ለሚያስተውል ሰው የክርስትና ጉዞ ሚስጢሩ ያለው ሁልጊዜ ክርስቶስን በመከተል፤ ከወደቁበት በፍጥነት በንስሐ በመመለስ፤ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላትና በእግዚአብሔር ጸጋ በመታመን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ለጴጥሮስ ጸጋውን ያበዛ ጌታ ሰውን የሚያሳድግበት መንገድ እንደ ሕንጻ ሠራተኛ በጡብ ላይ ጡብ በማስቀመጥ ነው ማለት ይቻላል። ዲዛይኑ በእጁ ነው። ተሰርቶ የሚያልቀውንም ሕንጻ አስቀድሞ አይቶታል። ስለዚህ በመልካምነቱ በሰው ሕይወት የሚሠራውን ከእርሱ ጋር በመስማማት ተሰርቶ ያለቀለት ቤት ለመሆን መሰራት ይገባል።





ምዕራፍ 7

# ጳውሎስ

ጳውሎስ ከብንያም ወገን የሆነ (ፊል 3፡5)፤ በተርሴስ የተወለደ አይሁዳዊ (ሐዋ 21፡39)፤ በኢየሩሳሌም በገማልያል እግር ሥር የተማረ (22፡3፤ 26፡4)፤ የሮም ዜግነት የነበረው (22፡28)፤ «ከዕብራዊም ዕብራዊ» (ፊሊ. 3፡5) የሆነ ለሕግም የሚቀና ፈሪሳዊ (ሐዋ 5፡34) የሕግ ምንነት ግን በትክክል ያልገባው ሰው ነበር። በ5 ዓ.ም. አካባቢ እንደ ተወለደ የሚገመተው ጳውሎስ በሰይፍ እስከ ተገደለበት እስከ 68 ዓ.ም. ድረስ ጌታ ለገለጠለት ወንጌል የታመነ፤ ያሳድድ የነበረውን ጌታ ያገለገለ፤ ለማፍረስ የተነሣውን ቤተ ክርስቲያን ያነጸ ታላቅ የወንጌል አገልጋይ፤ አስተማሪና ሐዋርያ ነበር።[20]

ጳውሎስ እስጢፋኖስ ሲወገር ያየና የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ ያሳድድ የነበረ ሰው ነበር (ሐዋ 7፤58፤ 8፡1-3፤ 22፡4)። ክርስቲያኖችን ለማሳደድ በነበረው ከፍተኛ «ቅናት» ለማሳሰር ወደ ደማስቆ ደብዳቤ ይዞ ሲሄድ በመንገድ ጌታ በድንገት የተገለጠለት ሰው ነው (ሐዋ 9፤ ገላ 1፡14፤ ፊል 3፡4-7)።

በደማስቆ መንገድ ጌታ ከተገለጠለት በኋላ ጳውሎስ ሕይወቱ ከመቅጽበት ተለወጠ፤ አቅጣጫውንም ቀየረ። ከዓይኑ ቅርፊት ሲወድቅለት ስለ ክርስቶስ ማንነት አጥርቶ ማየት ቻለ። እያሳደደ

[20] ይህ ምዕራፍ ከመልሳቸው መስፍን (2004 ዓ.ም.) *የዘላለም ክብር፡- የአዲስ ኪዳን ዓለት፡ አንድነት ማተሚያ ቤት፡* የተወሰደ ክፍል ይጨምራል።

የነበረውም ክርስቶስ ኢየሱስን መሆኑን ተገነዘበ:: ጽድቅ የሚገኘው ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በሕያው የእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መሆኑን ተረዳ::

ከደማስቆ በኋላ ጳውሎስ ለሚቀጥሉት አስር ዓመታት ያህል በተርሴስ አካባቢ እንደኖረ ይታሰባል:: መጀመሪያም በርናባስን ሲያገኘው ከእርሱ ጋር በመሆን በአንጾኪያ ለአንድ ዓመት ያህል ያገለግል ነበር:: ጳውሎስ በጌታ ለሐዋርያነት የተጠራና (ሐዋ 22:14-21፤ 26:16-18) ወደ አሕዛብ የተላከ ሰው ነው (ሐዋ 13:2-3፤ ሮሜ 15:16፤ 11:13):: ጴጥሮስን ለአይሁድ ሐዋርያ እንዲሆን አድርጎ የመረጠ ክርስቶስ ጳውሎስን ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያነት ሾመው (ገላ 2:7):: በዚህም አገልግሎቱ ከአይሁድ ውጭ ባሉ በሮም ግዛቶች ሁሉ እየተመላለሰ አገልግሏል::

ጳውሎስ ጌታን ካወቀ በኋላ መጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ከኬፋ (ጴጥሮስ) ጋር ለመተዋወቅ ነበር (ገላ 1:18):: በርናባስ ወደ ሐዋርያት አቀረበው፤ አስገባው (ሐዋ 9:26-28):: ጳውሎስ ከበርናባስ ጋር ከአንጾኪያ ወደ ኢየሩሳሌም ለሁለተኛ ጊዜ በመሄድ የሚሰብከውን ወንጌል «አዕማድ መስለው ለሚታዩት ለማስታወቅ» (ገላ 2:1-10) ከጴጥሮስ፤ ዮሐንስና ያዕቆብ ጋር ከተመካከሩ በኋላ ድሆችን እንዲያስቡ መክረዋቸው ወደ አገልግሎታቸው ተመለሱ:: ሐዋርያው ጳውሎስ አሕዛብን እያገለገለ ወደ ኢየሩሳሌምም በመምጣት ከሐዋርያት ጋር በመመካከር አሕዛብ ለመጽደቅ በክርስቶስ ማመን እንጂ መገረዝ እንደማያስፈልጋቸው ወደ ውሳኔ እንደ ደረሰ በሐዋ 15:1-29 እንመለከታለን::

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያገለግል መሠረትን ደግሞ ላለመመሥረት (ሮሜ 15:20) የተጠነቀቀ ሰው ነው:: ወንጌል ባልተሰበከባቸው ቦታዎች ወንጌልን ለማድረስ የወሰነና በማስተዋል ያገለገለ ሰው ነው:: የአሕዛብ ሐዋርያ ሆኖም በኢየሩሳሌም ራብ በነበረ ጊዜ





ከሚያገለግላቸው አብያተ ክርስቲያናት እርዳታን በማሰባሰብ በኢየሩሳሌም ያለችዋን ቤተ ክርስቲያን የደገፈ አገልጋይ ነው:: ጳውሎስ በአገልግሎቱ ምክንያት የታሰረ፤ የተገረፈ፤ የተራበ፤ ስለ ወንጌል ብዙ መከራ የተቀበለ ነገር ግን የደረሰበትን ሁሉ በደስታ የቆጠረና እስከ መጨረሻው የሮጠ ሰው ነው::

ጳውሎስ ወንጌልን መስበክ ሲጀምር የመጀመሪያው ስብከቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በመናገር ነበር (ሐዋ 9:20):: ጌታ ኢየሱስም በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ «ሰዎች እኔን ማን እንደ ሆንኩ ይላሉ?» ባለ ጊዜ የጴጥሮስ መልስ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» የሚል ነበር:: ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በዚህ እውነት ላይ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ማወቅና ማመን ይህንም መስበክ ታላቅ የወንጌል ስብከት ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ በአገልግሎቱና በስብከቱ አጉልቶ ይገልጥ የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፤ በመስቀል ላይ እንደ ሞተ፤ በሦስተኛውም ቀን እንደ ተነሣና መዳን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ብቻ መሆኑን ነበር:: ጳውሎስ የሕይወት ትርጉም የገባው ሰው ነበር:: መኖር ክርስቶስ እንደሆነ መሞትም ለእርሱ ጥቅም እንደሆነ ተገንዝቧል:: ስለዚህ ከሥጋ መጥፋት ከክርስቶስ ጋር መሆን እንደሆነ (2ቆሮ 5:8) እና ከክርስቶስ ጋር ለሁልጊዜ በደስታ እንደሚኖር (1ቆሮ 5:1-10) በመረዳት ይህን የሚያስተምር ሰው ነበር (ፊሊ 1:21-23):: «መኖር ክርስቶስ ነው» የሚለው ዋና መልእክቱ ስለ ሕይወት ያለውን ግንዛቤ ያሳያል::

እስጢፋኖስ በተወገረ ጊዜ ጳውሎስ የሰላሳ ዓመት ጎልማሳ እንደ ነበረ ይገመታል:: ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ ከቤት ወደ ቤት እየሄደ «የእግዚአብሔርም ቤተ ክርስቲያን ያለ ልክ አሳድድና አጠፋ ነበር» (ገላ 1:13) ይላል:: ማሳደድን በትጋት ያደርገው

እንደነበረ ሁሉ ወንጌል ሰባኪም ሲሆን ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ በጭካኔ አደረገው። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ሲያሳድድ ያለ እረፍት ነበር። ከአውርነት እንዲበራ ቅርፊት ተገፈፈለት። ዓይኑ ከበራለት በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ለመሥራት ሌሊትና ቀን ተግቷል። በእውነት የተለወጠ ሕይወት ያለው ሰው በቀደመው የጨለማ ዘመኑ ለከፋ ያውለው የነበረውን ትጋት ለመልካም ያውለዋል።

ጳውሎስ በጉዞውና በአገልግሎቱ ስለ ክርስቶስ ብዙ መከራ ተቀብሎአል። አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ተገርፎአል፤ ሦስት ጊዜ በበትር ተመቷል፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሮአል፤ መርከቡ ሦስት ጊዜ ተሰብሯል፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖሯል፤ ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄደ፤ በብዙ በሚያስፈሩ ሁኔታዎች ውስጥ አለፈ፤ እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበረ። ሰዎች ሐዋርያነቱን ተቃውመዋል፤ በፊልጵስዩስ፤ ኢየሩሳሌም፤ ቂሳርያ፤ ሮም ታስሮአል። ይህ ሁሉ ሆኖ እርሱ የሚለው ግን «...ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው» (2ቆሮ 11:23-29)። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛውን ጊዜ ለኑሮውና አገልግሎቱ የሚያስፈልገውን የሚያሟላው ድንኳን እየሰፋ ነበር (ሐዋ 18:3)።

እንዲሁም ጳውሎስ «የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ» (2ቆሮ 12:7) የሚለው ‹የሥጋ መውጊያ› ነበረው። ይህ መውጊያ ምን እንደ ነበረ በውል ባይገለጽም የሥጋ ፈተና (ሮሜ 7:14-25)፤ የዓይን ሕመም ችግር (ገላ 5:15)፤ የንግግር ችግር (2ቆሮ 10:10) ወይም ከባድ ሕመም ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል። ከእርሱ እንዲወሰድ ጸለየ፤ የተሰጠው መለኮታዊ መልስ «ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና...» (2ቆሮ 12:8-9) የሚል ነበር።





የእግዚአብሔር መንፈስ ጳውሎስንና በርናባስን «ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ» ብሎ ሲጠራቸውና ሲለያቸው በሐዋ 13:1-3 እንመለከታለን። ከዚህ በኋላ ጳውሎስ የአገልግሎት (ሚሲዮናዊ) ጉዞዎችን እንዳደረገ ከመጽሐፍ ቅዱስ እናስተውላለን። በዚህም ከበርናባስ፤ ከሲላስ፤ ከጢሞቴዎስ፤ ከቲቶና ከሌሎችም ጋር አብሮ አገልግሎአል። በአገልግሎት ጉዞው በተለይ ጢሞቴዎስ ለጳውሎስ ጠቃሚ ረዳት ሆኖለታል።

ከ47 ዓ.ም እስከ 62 ዓ.ም በነበሩት 15 ዓመታት መነሻውን ከአንጾኪያ (ሶሪያ) ያደረገ ሦስት ዙር የወንጌል ጉዞዎች አድርጓአል። እንዲሁም ወደ ሮም ሄዷል። በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ 1400 ማይል (2240 ኪሎ ሜትር)፤ በሁለተኛው 2800 ማይል (4480 ኪሎ ሜትር)፤ በሦስተኛው 2700 ማይል (4320 ኪሎ ሜትር)፤ ወደ ሮም ባደረገው ጉዞ 2250 ማይል (3600 ኪሎ ሜትር) በድምሩ 6150 ማይል (14640 ኪሎ ሜትር) በምድርና በባሕር የተጓዘ ትጉ ሐዋርያ ነበር። ከእነዚህ ሌላ ብዙ ጉዞዎች እንዳደረገ ይታወቃል።[21] ሦስቱን ጉዞዎች በአጭሩ እንመለከት።

## የመጀመሪያ የአገልግሎት ጉዞ

ጳውሎስ የመጀመሪያ የአገልግሎት ጉዞውን (ሚሲዮናዊ ጉዞ) የጀመረው ከበርናባስ ጋር *በመንፈስ ቅዱስ ተልከው (13:4)* ከአንጾኪያ ወደ ሴሌውቅያሲሄዱ ነው። ዮሐንስ የተባለው ማርቆስ (ማር 12:25) አብሮአቸው ነበረ፥ በኋላ እነርሱን ትቶ ከመንገዱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ (ሐዋ 13:13)።

በዚህ ጉዞው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ጉባኤ ላይ ተገኝቶ (ሐዋ 15፤ ገላ 2) ደኅንነትን ለማግኘት አሕዛብ መገረዝ እንደማያስፈልጋቸው

[21] የጉዞው ርዝመት ስሌት የተወሰደው Rose Publishing (2006); Torrance, CA.

አስረዳ:: በዚህም ሁሉም ወደ መረዳትና መግባባት ደረሱ:: አዕማድ የሆነው ጴጥሮስ (ኬፋ) አይሁድን በመፍራት ያደርግ ስለነበረው ድርጊት ጳውሎስ ፊት ለፊት ተቃውመው (ገላ 2:11-14):: ጳውሎስ በዚህ ጉዞው ወንጌልን ሰብኮአል፤ የሚያምነውን በጉባኤ ተገኝቶ አስረድቶአል፤ በስህተት መንገድ የነበሩ ታላላቅ የሚባሉትን ሳይቀር ተቃውሞ እውነት የሆነውን አስተምሮአል::

## ሁለተኛው የአገልግሎት ጉዞ

ጳውሎስ ቀደም ሲል በሄደባቸው ቦታዎችና ወደ ተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት ተመልሶ በመሄድ ለመጠየቅና ለማጽናናት ያስባል:: በዚህ በሁለተኛው አገልግሎት ጉዞው የቡድን አባላት ጳውሎስ፤ ሲላስ፤ ጢሞቴዎስና ሉቃስ ሆነዋል:: በርናባስ ደግሞ ከማርቆስ ጋር ሆነ (ሐዋ 15:24-39):: ይህ ጉዞ የአራት ሰዎች የቡድን አገልግሎት ሲሆን ወጣቱ ጢሞቴዎስ የጌታ ደቀ መዝሙር የሆነች የአንዲት አይሁዳዊት ልጅ ነበር:: ጢሞቴዎስ ከወጣትነቱ ጀምሮ ከጳውሎስ ጋር የነበረና በኋላም አደራ የተቀበለ ሰው ነው::

በሁለተኛ ጉዞው አንድ ለየት ያለ ነገር ይታያል:: ጳውሎስ ቃሉን እንዳይናገር መንፈስ ቅዱስ እንደከለከለው ሊሄድ ወዳሰበውም እንዲሄድ እንዳልፈቀደለት ነገር ግን ወዴት መሄድ እንደሚገባው በራእይ እንደተረዳ ከሐዋ 16:6-10 እንገነዘባለን:: ከዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድና አመራር የጳውሎስ'ንም መታዘዝ እናስተውላለን::

በዚህ ጉዞው ጳውሎስ ከሲላስ ጋር በፊልጵስዩስ ታስሮ ነበረ:: እግዚአብሔርም የመሬት መናወጥን በማምጣት ከእስር ፈታቸው፤ በዚህም ወንጌል ወደ ብዙዎች ደረሰ (ሐዋ 16):: እንዲሁም ጳውሎስ በቆሮንቶስ በቆየበት ጊዜ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር በመሆን ለመኖሪያው እየሠራ (ድንኳን እየሰፋ) ይኖር ነበር (ሐዋ 18)::





የሁለተኛ ጉዞውን ሲጨርስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅዱሳንን ካገኘ በኋላ እንደገና ወደ አንጾኪያ ተመለሰ (ሐዋ 18:22)::

## ሦስተኛው የአገልግሎት ጉዞ

የጳውሎስ ሦስተኛው የአገልግሎት ጉዞ ከሐዋ 18:23-21:17 ይገኛል:: በዚህ ጉዞው ደቀ መዛሙርትን እያጸና (ሐዋ 18:23) ሄደ:: እንዲሁም በኢየሩሳሌም ራብ ስለ ነበረ ስለ ቅዱሳን ስለሚሰበሰበው እርዳታ መመሪያ ሰጠ (1ቆሮ 16:1-2):: በሦስተኛ ጉዞው በቲቶ ወደ እርሱ መምጣት ተጽናና (2ቆሮ 7:6) ጢሞቴዎስም አብሮት ነበረ:: በዚህኛው ጉዞ በኢየሩሳሌም ታስሮ እንደ ነበረና በፊልክስ፤ በፊስጦስ፤ በአግሪጳ ፊት ለፍርድ እንደ ቀረበ ከዚያም ወደ ሮም እንደ ተላከ እናነባለን::

ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ገና እንደ ታሠረና በዚህም ጊዜ አንዳንዶች እንደ ተዉት በተለይም ዴማስ «ይህን ዓለም ወዶ ትቶኛልና» (2ጢሞ 4:10) በማለት ብቸኝነቱን ይገልጻል:: ከእርሱ ጋር የቀረው ሉቃስ ብቻ ነበረ (1ጢሞ 4:11):: አብረውት የተሰለፉ ብዙ ነበሩ፤ እስከ መጨረሻ የቀጠሉት ግን ጥቂቶች ናቸው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ መጨረሻው ባለው የሚናገረው «መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፤ ሩጫውን ጨርሼአለሁ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል» (2ጢሞ 4:7-8) በማለት ነበር::

ጳውሎስ በቃልና በኑሮ በጽሑፍም ጭምር ወንጌልን አገልግሏል:: በወንጌል ጉዞዎቹ ለተከላቸው አብያተ ክርስቲያናት፤ ላገኛቸው ሰዎች፤ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች፤ ወደፊትም ሊሄድባቸው ወደሚያስባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀር መልእክት ልኳል:: ወንጌልን በጽሑፍ አስተምሮአል:: ለጥያቄዎች መልስ፤ ለአገልግሎት መመሪያ ሰጥቶአል፤ አስጠንቅቋል፤ መክሮአል:: ከሃያ ሰባቱ የአዲስ

ኪዳን መጻሕፍት መካከል አሥራ አራቱን (የዕብራውያንን መልእክት ጨምሮ) የጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው።

የሐዋርያው ጳውሎስን ሕይወትና አገልግሎት ስንመለከት ስለ ክርስቲያናዊ አመራር የሚከተሉትን ነጥቦች ልናጤን እንችላለን።

1. ጳውሎስ ግልጽ ዓላማ ያለው የወንጌል አገልጋይ፡፡
ሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት ምን እንደሆነ፣ በምድር ላይ ለምን እንደሚኖርና በሕይወት እስካለ ድረስ ደግሞ ማድረግ ያለበትን አበጥሮ ተረድቷል፡፡ ስለሆነም «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና» (ፊል 1:21) በማለት ዓላማውን በግልጽ ያስታውቃል፡፡ እንዲሁም «ይህ ናፍቆቴ ተስፋዬም ነውና ...ክርስቶስ ...በሥጋዬ ይከብራል» (ፊል 1:20) በማለት በአጽንዖት ይገልጻል፡፡ ዓላማው ሕይወት ነው፣ ትንሣኤን ማግኘት ነው፣ ክርስቶስን መምሰል ነው፣ ክርስቶስን ማክበር ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ሁሉን ነገር በሚዛን አስቀምጦ በመመዘን ለሰው «ረብ» ወይም ጠቃሚ የሚመስለውን ነገር ሁሉ እንደ ትንሽ (ጉድፍ) ቆጠረው፡፡

ጳውሎስ በሕይወት ዘመኑ ሁለት ዓይነት ቅንዓቶች ነበሩት፡፡ አንደኛው ከሐዋ 9 በፊት የነበረው ቅንዓት ነው፡፡ ያ ዘመን ለጳውሎስ ለሃይማኖቱ ቀናተኛ በመሆን ክርስቲያኖችን ያሳደደበት የቀናተኛነት ዘመን ነበር (ፊል 3:5)፡፡ ይህ «ሕይወት» የሌለበት የሃይማኖተኛነት ቅንዓት በእርሱ ላይ የቆየው በደማስቆ መንገድ ጌታ ኢየሱስን እስካገኘበት ጊዜ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ከንቱ ቅንዓት ሆኖ ተቆጠረ፡፡ ሁለተኛው ቅንዓት ደግሞ ክርስቶስን ለማወቅ፣ እርሱንም ለመምሰል የመናፈቅ ቅንዓት ነው፡፡ ይህ ቅንዓት እግዚአብሔርን የሚያከብር ቅንዓት ነው፡፡





ሐዋርያው ጳውሎስ ፅኑ ዓላማና ቅንዓት ስላለው «እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ» (ፊል 3:10) በማለት ያላቋረጠ ናፍቆቱን ይገልጻል፡፡ በምድር ላይ መኖር ማለት ክርስቶስ ማለት እንደሆነ፣ መሞትም ለእርሱ የበለጠ ጥቅም እንደሆነ ስለተረዳ በእነዚህ በሁለት ጥሩ ምርጫዎች መካከል ያለውን ትግል ሲናገር «በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፡- ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፣ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፣ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው» (1:23) ይላል፡፡ በሕይወት በምድር ላይ ከሚኖር ይልቅ ወደ ጌታ መሄድ የተሻለ እንደሆነ አውቆ መሄዱን እየወደደ ይናፍቃል፣ ሆኖም በምድር እስካለ ድረስ ደግሞ የሚኖርበት ምክንያት ሰዎችን ለመጥቀም እንደሆነ ይህን ተገንዝቦአል፡፡

ጳውሎስ የክርስቶስ እንጂ የራሱ (የጳውሎስ) እንዳይደለ የተረዳ ሰው በመሆኑ «እኔ የኢየሱስን ማህተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድስ እንኳን አያድክመኝ» (ገላ 6:17) በማለት ቁርጥ ዓላማውን ይናገራል፡፡ እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ «አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፡፡ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም» (ገላ 2:20-21) ይላል፡፡ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጸጋ አክብሮ የያዘው ክርስቶስ በእርሱ ስለሚኖር ነው፡፡ ጳውሎስ የሕይወት ትርጉም ገብቶታል፡፡

እንግዲህ ክርስቲያን መሪ ለሕይወቱ ግልጽ ዓላማ ያለው ሰው ሊሆን ይገባል፡፡ የክርስቲያን ሁሉ ትኩረት አንድ ዋና ነገር ላይ ሊሆን ይገባል፣ ይህም ክርስቶስን በኑሮ ሁሉ በማክበር በእርሱ የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት ማግኘት ነው፡፡ በኑሮው የሚመጡ

ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ ከዚህ አንጻር መመዘን ይገባዋል:: ክርስቲያን መሪ ስለ ራሱ ማንነትና የሕይወት ትኩረት የጠራ ግንዛቤ ያለው መሆን አለበት:: ይህም ማለት እርሱ የክርስቶስ መሆኑንና ዓላማውም የክርስቶስን ሀሳብ ማገልገል እንደሆነ መገንዘብ ይኖርበታል:: ውጤታማ መሪዎች ለራሳቸው ግልጽ የሆነ የሕይወት ዓላማ ኖሮአቸው ሌሎችን በዚህ ዓላማ የሚመሩ ናቸው::

## 2. ጳውሎስ ለአገልግሎት የተሾመ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ::

ጳውሎስ ለወንጌል አገልጋይነት በጌታ የተሾመ ነው (ኤፌ 3:7፤ ቆላ 1:23፤ 1ጢሞ 1:12፤ 2ጢሞ 1:11):: ጳውሎስ ስለ ተባለው ሳውል ጌታ ኢየሱስ «ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና» (ሐዋ 9:15) ብሎአል:: የጳውሎስ ጥሪ ወንጌል ሰባኪነት፤ ሐዋርያነትና፤ አስተማሪነት ነው (2ጢሞ 1:10-11):: ወንጌልን ለአሕዛብ መስበክ ዋና ጥሪው እንደሆነ ያውቃል (ገላ 1:16):: የአገልግሎቱ ትኩረት «የእግዚአብሔር ምስጢር የሆነውን ክርስቶስን ለማስታወቅ» (ቆላ 2:2) እንደሆነ ይገልጻል::

ጳውሎስ ጌታን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እያስረገጠ መስበክና ማስተማር ጀመረ (ሐዋ 9:20-22):: ይህንንም አገልግሎቱን አክብሮ በትጋት የሚሠራ ሰው ነበር (ሮሜ 11:13):: «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ» (1ቆሮ 9:16) እንደሚል አገልግሎትን በትጋት አለመፈጸም እግዚአብሔርን መበደል ወይም በእርሱ ላይ ማመፅ (ኃጢአትን ማድረግ) እንደሆነ አስተውሏል:: «ወዮልኝ» ማለቱም የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ባይጨርስ ተጠያቂ እንደሚሆንና በእርሱም ላይ ፍርድ እንደሚኖርበት በመረዳቱ ነው:: ስለሆነም ወንጌልን ለማገልገል የማይደክመው ሰው ነበር:: በሁሉም ስፍራ፡- በእስር





ቤት፤ በባሕርም ላይ፤ በመርከብ ላይ፤ በቤተ መቅደስ፤ በወንዝ ዳር፤ ወዘተ. ይሰብክ ነበር::

ጳውሎስ በጻፋቸው መልእክቶች ሲያስተዋውቅ የክርስቶስ ባሪያ (ሮሜ 1:1፤ ፊል 1:1፤ ቲቶ 1:1) በማለት ራሱን ጠርቶአል:: ሐዋርያ ነው፤ ደግሞም ባሪያ ነው:: «ባሪያ» ለማለት የተጠቀመበት የግሪክ ቃል «ዱሎስ»[22] የሚለውን ሲሆን የሚያመለክተውም በፈቃዱና በሕግ ራሱን ለጌታው ያስገዛ (የሰጠ) ባሪያ የሚለውን ሀሳብ ሲሆን ይህም በዘዳ 15:1-23 ከተገለጸው ጋር ይስማማል:: ጳውሎስ በፍቅር (በውዴታ) ራሱን ለጌታው ያስገዛ አገልጋይ ነው::

ክርስቲያን መሪ ከሁሉ አስቀድሞ በሥራው ባለቤት በእግዚአብሔር ለቦታው የተጠራ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት:: እግዚአብሔር ሲጠራ ማንን? ለምን ዓይነት አገልግሎት? በየት አካባቢ? መቼ? የሚለውን ሁሉ የሚወስን እርሱ ነው:: ይህን የተገነዘበ ክርስቲያናዊ መሪ የተጠራው እግዚአብሔር ያሰበውን ለማድረግ ምክንያት ወይም መገልገያ መሣሪያ የሚሆን የእርሱ ዕቃ መሆኑን መዘንጋት የለበትም:: ማረሻ ወይም ማጭድ በገበሬ እጅ እንደሚሆን እንዲሁ አገልጋይ (መሪ) በእግዚአብሔር እጅ ነው:: ክርስቲያናዊ መሪ ለአገልግሎት የተመረጠ የክርስቶስ ባሪያ ነው::

## 3. ጳውሎስ ባለው ደስ የሚለው በተሰጠው መጠን የሚኖር ሐዋርያ::

ሐዋርያው ጳውሎስ ደስታው የተመሠረተው በእግዚአብሔር ማንነት ላይ ስለሆነ እርሱ በሰጠው መጠን በደስታ ይኖር ነበር::

[22] "Doulos" - signifies a servant who has willingly and legally bonded himself to a master.

ሐዋርያው ስለ ኑሮና እርካታ[23] ያለውን ግንዛቤ «...የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለት ተምሬአለሁና መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና፤ መራብንም መብዛትንና፤ መጉደልን ተምሬአለሁ[24]» (ፊሊ. 4፡11) በማለት ገልጾአል:: ጳውሎስ በሕይወቱ ተማርሁ የሚለው አንዱ ነገር «የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን» ነው:: ያሳለፈው ኑሮ መጥገብም ነበረበት፤ መራብም ነበረበት፤ ጉድለት ነበረው፤ የበዛለትም ጊዜ ነበረ:: «ያለኝ ይበቃኛል» ማለት ትልቅ መንፈሳዊ መረዳት ነው::

በሰው ሕይወት ማግኘትም ማጣትም ይኖራል:: በዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔርን ስለ እርሱነቱ ማመስገንና በእርሱ ደግሞ ደስ መሰኘት ከፍ ያለ የመማር ደረጃ ነው:: አንድ ሰው በአንድ በተወሰነ ጊዜ ይብዛም ይነስ በእጁ ያለው ነገር ከሚወደው አባቱ ከእግዚአብሔር ለዚያ ወቅት የተሰጠው (የተለቀቀለት) እንደሆነ የሚያስተውል ባለው መጠን ላይ ሳይሆን ለዘላለም በወደደው አባቱ እግዚአብሔር ደስ ይሰኛል:: ያንን ያህል ለዚያ ዘመን የሰጠ እግዚአብሔር በሌላ ወቅት ደግሞ ቢወድ አብዝቶ ይሰጣል::

ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጓል (1ቆሮ 9፡14):: ሆኖም ወንጌልን የሚሰብኩበት ዓላማ ቀለብን ለማግኘት ብለው ሳይሆን ወንጌልን በታማኝነት ሲሰብኩ አንዱ ፍሬ ከወንጌል ቀለባቸውን ማግኘት ነው:: ይህም «በመቅደስ የሚያገለግሉ ከመቅደስ የሆነውን ነገር እንዲመገቡ» (1ቆሮ 9፡13) እንዳለው ነው:: ካህናት በመቅደስ ያገለግሉ የነበሩት ቀለብ ያገኙ ዘንድ ሳይሆን ሰዎች የመቅደሱን ጌታ እግዚአብሔርን በመስጠት

[23] Contentment

[24] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ማጣትን አውቃለሁ ማግኘትንም አውቃለሁ፡ በጠግበም ሆነ በራብ ባገኝም ሆነ ባጣ በማናቸውም ሆነ በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተምሬአለሁ»





ለማምለክ ስጦታ ሲያመጡ ለአገልጋዮችም ቀለብ ይተርፋቸው ነበር::

ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ጊዜ ለምን ወደ ቆሮንቶስ መሄድ እንደሚፈልግ ሲጽፍ «እነሆ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ ስዘጋጅ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ አልከብድባችሁምም፤ እናንተን እንጂ ያላችሁን አልፈልግምና:: ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና:: «እኔ ግን ስለ ነፍሳችሁ በብዙ ደስታ ገንዘቤን እከፍላለሁ፤ ራሴን እንኳን እከፍላለሁ»[25] (2ቆሮ 12፡14-15) ይላል:: ወደ ቆሮንቶስ መሄድ የፈለገው ከእነርሱ ጥቅም (ገንዘብ) ለማግኘት ሳይሆን ሰዎቹን ራሳቸውን ፈልጎ ነበር:: ከሚያገለግላቸው ሰዎች ስለሚያገኘው ጥቅም በማሰብ በዚህ ዓላማ የሚያገለግል ሰው ቀዳሚ ትኩረቱ የሰዎቹ ጤናማ የሕይወት እድገት ሳይሆን ብዙ ገንዘብ የሚሰጡበትን ስልት መፈለግ ነው::

በሌላም ስፍራ «ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤ እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ» (ሐዋ 20፡33) ይላል:: ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ጥቅምን የማይፈልግ የወንጌልን የምሥራች በነጻ ለማገልገል የቆረጠ ሰው (1ቆሮ 9፡18-25) ነው:: ወንጌልን በትጋት የሚያገለግለው ጥሪውን ለመፈጸም ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በኑሮውና በአካሄዱ ጠንቃቃ ሰው ነው::

እንግዲህ በእግዚአብሔር ደስ የሚለው ክርስቲያናዊ መሪ እርሱ በሰጠው (በለቀቀለት) መጠን የሚኖር ሰው ነው:: ደስታው የተመሠረተው በእግዚአብሔር ላይ ነው:: መሪ እግዚአብሔር ለእርሱ ያልሰጠውንና በሌላ ሰው እጅ የሚያየውን የማይመኝ፤

[25] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «ወደ እናንተ ለመምጣት ስዘጋጅ ይህ ሦስተኛዬ ነው:: ስመጣ በምንም ነገር ሸክም አልሆንባችሁም:: እኔ እናንተን እንጂ ከእናንተ ምንም አልፈልግምና ደግሞም ወላጆች ለልጆች ገንዘብ ያከማቻሉ እንጂ ልጆች ለወላጆች አያከማቹም»

ይልቁን ባለው የሚረካና እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ነው:: የራሱን ኑሮ ለማሻሻል በሚል ዋና ዓላማ ወደ ወንጌል አገልግሎት የሚገባ ወይም በዚህ ዓላማ በአገልግሎት ላይ የተሰማራ ሰው ከተሰመረው መስመር ውጭ በከንቱ የሚሮጥን ሯጭ ይመስላል::

## 4. ጳውሎስ:- በፍቅር የሚያገለግልና የቅዱሳንን አንድነት የሚያንጽ መሪ::

ጳውሎስ ፍቅር የጸጋ (የአገልግሎት) ስጦታዎች ሁሉ መሠረት እንደሆነ የተገነዘበ ሰው ነው:: ስለዚህም ሲጽፍ በልሳን መናገር፤ ትንቢት መናገር፤ የእምነት ሰው መሆን፤ ቸርነትን ማድረግ (1ቆሮ 13:1-3) ያለ ፍቅር አገልጋዩን ምንም አይጠቅመውም ብሏል:: ይህም ማለት አገልግሎት - (ሲቀነስ) ፍቅር = 0 (ዜሮ) ማለት ነው:: ከዚህ ዓይነት አገልግሎት የሚያገለግለው ሰው የሚያተርፈው ነገር አይኖርም ማለት ነው::

ጳውሎስ የፍቅርን ምንነት የተገነዘበ ስለሆነ በ1ተሰ 2:1-12 ባለው ክፍል እንደሚታየው ለተሰሎንቄ ሰዎች ያለውን አገልግሎቱን በአባት (2:12)፤ በወንድምና (2:1፤9) በሞግዚት (2:7) ምሳሌ አድርጎ «እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ...ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና» (2:8) በማለት ይገልጻል:: ይህ በፍቅር መምራት ነው:: አገልግሎቱ ወንጌልን መስበክ ነው፤ የሚሰብክላቸው ሰዎቹን በመውደድ ነው::

በሌላም ስፍራ «የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል» (2ቆሮ 5:14) ሲል የሚያደርገውን ያደርገው ዘንድ አስገዳጁ ኃይል ክርስቶስን መውደዱ ነው:: ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈውም መልእክቱ አገልጋዮች «እውነትን በፍቅር» (ኤፌ 4:15) የሚናገሩ እንዲሆኑ አስተምሮአል::





ጳውሎስ የፍቅር ሰው ስለሆነ ወንድሙን በስህተት መንገድ ቢያየው ያቀናዋል:: ጳውሎስ አይሁድን በመፍራት የሚያደርገውን ባየ ጊዜ ጴጥሮስን «ፊት ለፊት ተቃወምሁት» (ገላ 2:11) ይላል:: የግብዝነት (የማስመሰል) መንገድ ነበረና:: እንዲሁም «በርናባስ ስንኳ በግብዝነታቸው እስከ ተሳበ ድረስ፤ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ:: ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን ...አልሁት» (2:13-14):: ለጳውሎስ መለኪያው «የወንጌል እውነት» ስለሆነ ለዚህ እውነት «ታማኝ» ነበር:: ጳውሎስ ሰዎችን የሚወቅሳቸው በነበረው የሐዋርያዊ ሥልጣን ታብዮ ሳይሆን መወቀስ የሚገባቸው ስለ ነበረ ነው (ገላ 2:11):: ለእውነት ታማኝ የሆነ ደግሞ ሰውን አይፈራም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ደፋር የወንጌል አርበኛ ነው::

መሪ የሚያደርገው አገልግሎት ሁሉ በፍቅር መሠረት ላይ ያረፈና ስለ ፍቅር የሚደረግ መሆን አለበት:: ስለዚህ ለአገልግሎት ቀዳሚው ምክንያት ፍቅር ሲሆን ተግባር ተከታይ ነው:: እንዲሁም እውነተኛ ፍቅር ባለበት መተራረም፤ መመካከር ይኖራል:: በአገልጋዮች መካከል ግብዝነትን (ማስመሰልን፤ ያልሆኑትን መሆንን) እያዩ የማይገስጽና የማያስተካክል መሪ ለወንጌል እውነት ታማኝ ያልሆነ ሰው ነው::

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የተፈጠረች «አዲስ ሰው» (ኤፌ 2:15)፤ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የአካሉ ክፍል (ብልት) የሆኑላት አንድ አካል ናት:: «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ 3:28) «...አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና» (ሮሜ 10:12):: «...እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል» (1ቆሮ 12:13):: ቤተ ክርስቲያን ‹የስመጥር ሰዎች› ወይም የመሪዎች

ሳትሆን የክርስቶስ ናት፡፡ በልዩ ልዩ ቡድን የተከፋፈለች ሳትሆን አንድ የክርስቶስ አካል ናት፡፡

መከፋፈል የክርስቶስን መስቀል ትርጉም አለመረዳት የሚያስከተለው ችግርና (1ቆሮ 1:18-2-5) የሥጋዊነት ምልክት ነው (1ቆሮ 3:1-4)፡፡ መከፋፈል መንፈሳዊ እድገትን ይገታል (3:1-9)፤ ብድራት ማጣትን ያስከትላል (3:10-4:5)፡፡ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለሆነች መከፋፈል የእርሱን ቤተ መቅደስ እንደ ማፍረስ ነው (3:16-17)፡፡

በዚህ ረገድ የመሪዎች ድርሻ ትልቅ ነው፡፡ መሪዎች የራስ ተከታዮቻቸውንና ቡድኖቻቸውን ባለማፍራትና ምናልባትም አንዳንዶች «እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ ...እኔ የአጵሎስ ነኝ» (1ቆሮ 3:4) የሚሉ ቢኖሩ በፍቅር በማቅናት የቤተ ክርስቲያንን የመንፈስ ኅብረት መጠበቅ ይገባቸዋል፡፡ ስለሆነም መከፋፈልና መጠላላት ሳይኖር የመንፈስን አንድነት በሰላም ማሰሪያ መጠበቅ ይገባል፡፡

### 5. ጳውሎስ በእግዚአብሔር የሚታመን ትሑት ሐዋርያ፡፡

ጳውሎስ እግዚአብሔር ከየት እንዳነሣው የማይረሳና በደረሰበት ከፍተኛ የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ የማይታበይ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚሰጥ ሐዋርያ ነበር፡፡ የደረሰበትን ደረጃ የደረሰው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ብቻ እንደሆነ በተደጋጋሚ ይናገራል፡፡ በኤፌ 3:8 «...ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ ተሰጠ» ይላል፡፡ እንዲሁም በ1ቆሮ 15:9 «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ» ይላል፡፡





ጳውሎስ ጌታን ከማወቁ በፊት ከነበረው ኑሮ አሁን ሐዋርያ ወደሆነበት ሕይወት ያሸጋገረው ድልድይ የእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ እንደሆነ አይረሳም፡፡ ይህ የተሻገረበትን ድልድይ ያልሰበረ ትምክህቱ የእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ ብቻ የሆነ ሰው ሲናገር «ተሳዳቢና፤ አሳዳጅ፤ አንገላችም ምንም ብሆን ...ምሕረትን አገኘሁ፤ የጌታችንም ጸጋ ...በዛ» (1ጢሞ 1:13-14) ይላል፡፡ እንዲሁም «ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ ...ምሕረትን አገኘሁ» (1ጢሞ 1:16) በማለት ይገልጻል፡፡

የጳውሎስ ተቃዋሚዎች «...ሰውነቱ ግን ሲታይ ደካማ ነው፤ ንግግሩም የተናቀ ነው» (2ቆሮ 10:10) በማለታቸው ሰዎች ለመሪነት የሚመለከቱት ‹ካሪዝማ› የለውም ይሉት ነበር፡፡ ጳውሎስ ግን በአፈጣጠሩ ላይ አያጉረመርምም፤ የተሰጠውንና ሊለውጠው የማይችለውን በምስጋና ተቀብሎ እርሱ ሊያደርግ በሚገባው ግን ጥንካሬው በመልእክቶቹ ብቻ ሳይሆን በተግባርም መሆኑን ያስረዳል፡፡

ትሑቱ ጳውሎስ መልካም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሚሰጥ የተረዳ ሰው በመሆኑ «ያልተቀበልከው ምን አለ?» (1ቆሮ 4:7) በማለት ባላቸው ነገር የሚመኩትን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም «ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ ነገር ግን የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ» (1ቆሮ 1:29) ይላል፡፡ ምክንያቱም «ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና፤ ጽድቅ፤ ቅድስናም፤ ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው» (1:30-31)፡፡ ሰው አለኝ የሚለው ነገር መንፈሳዊውም ሆነ ሥጋዊው/ ቁሳዊው ሁሉም ከእግዚአብሔር የተሰጠው ነው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ በገማልያል እግር ሥር የተማረ ከፍተኛ እውቀት ያለው ሰው ሆኖ ሳለ ለአገልጋይነት ብቃት እንደሌለው ብቃቱ እግዚአብሔር እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በ2ቆሮ 3:5 «ብቃታችን

ከእግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም» ይላል፡፡ እንዲሁም «ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ለእነዚያም ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን፡፡ ለዚህም ነገር የሚበቃ ማን ነው?» (2ቆሮ 2፡16) ይልና ለሕይወት ሽታ ለመሆን ሰው እንደማይበቃ እግዚአብሔር ግን ሰውን ለሕይወት ሽታ እንዲሆን ብቁ እንደሚያደርገው ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም የሰውን ደካማነት ሲገልጽ «ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን» (2ቆሮ 4፡7) ብሏል፡፡ ስለሆነም የአገልጋይ ብቃቱ እግዚአብሔር ነው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል አገልግሎት ከሌሎች አገልጋዮች ይልቅ በብዙ ያገለገለ ቢሆንም «...ከሁላችሁ ይልቅ ግን ደከምሁ፣ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም» (1ቆሮ 15፡10) በማለት ክብርን ለእግዚአብሔር ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የሆነውን ሁሉ ከራሱ እንዳልሆነ በማስተዋሉ «ክርስቶስ በእኔ አድሮ እንዲናገር» (2ቆሮ 13፡3) ይላል፡፡

ትሕትና በእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ መመካት ነው፡፡ መሪ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ ለመሆኑ አንዱ ምልክት ትሕትናን ሲጎናጸፍ ነው፡፡ ሰው ሁሉ እንደ ሸክላ ዕቃ አቅም የሌለው፤ የከበረውን መዝገብ መሸከም የማይችል ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ሰው የእርሱን የከበረ መልእክት ተሸክሞ እንዲዞር በታላቅ ጸጋም እንዲያገለግል ያስችለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የአገልግሎቱ ፍሬ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ እንጂ ከራሱ በሆነ እውቀት፣ ጥበብ ወይም ችሎታ እንዳልሆነ የተገነዘበ አገልጋይ ከትዕቢት የራቀ ሰው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋና ትዕቢት ይቀዋወማሉ፡፡ ስለሆነም የአገልጋይ አቅሙና ብቃቱ እግዚአብሔር ነው፡፡ «የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ» (1ቆሮ 1፡30)፡፡





## 6. ጳውሎስ በጽድቅ የሚኖር፤ በምሳሌነት የሚመራ አለቃ፡፡

በክርስትና ምሳሌ መሆን ማለት የክርስቶስን ባሕርይ በሰዎች መካከል መግለጥ ወይም በመኖር ማሳየት ነው፡፡ ሕዝብ የመሪውን ቃል ብቻ ሳይሆን ተግባሩን ይመለከታልና መሪ የሚያስተምረውን ራሱ በመኖር ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር ፈሪሳውያን «ያዘዟችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፤ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ» (ማቴ 23፡3) በማለት ሕዝቡን አስተማረ፡፡ ይህም የፈሪሳውያን ንግግር እንደ ሕጉ ትክክል ነው፤ ተግባራቸው ግን ስህተትና የተናገሩትን የሚቃረን አፍራሽ ነበር፡፡ ንግግሩና ተግባሩ የሚጋጩበት ሰው «ግብዝ» ነው፡፡ የግብዝነት ኑሮ ለመልካም ሕይወት ምሳሌነት የለውም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ እርሱ ክርስቶስን በመምሰል የምሳሌነት ሕይወት እንደኖረ ሁሉ ሌሎች አገልጋዮች ሁሉ ለሚያምኑት ምሳሌ እንዲሆኑ ይመክራል፡፡ በአገልግሎት የሚያሳድገውን ቲቶን «በነገር ሁሉ መልካም በማድረግ ምሳሌ በመሆን ራስህን አሳይ» (ቲቶ 1፡7) ብሎታል፡፡ ጢሞቴዎስን «በቃልና በኑሮ፤ በፍቅርም፣ በእምነትም፣ በንጽሕና ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ- ማንም ታናሽነትህን አይናቀው» (1ጢሞ 4(11-12) አለው፡፡

ወጣቱ ጢሞቴዎስ ከግብዝነት የራቀ፤ የሚናገረውና የሚኖረው የተመሳሰለ፤ የማይጋጭ ይሆን ዘንድ በቃልና በኑሮ ምሳሌነት ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም ለሚያምኑት ሁሉ አርአያ እንዲሆን ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክረው የራሱን ምሳሌነት በመጥቀስ «በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነትና ፍቅር አድርገህ ከእኔ የሰማኸውን ጤናማ ቃል ምሳሌ አስብ» (2ጢሞ 1፡13) ይለዋል፡፡ ጳውሎስ

መልካም የሆነውን ነገር ለሌሎች ሠርቶ-የሚያሳይ፤ በመልካም አኗኗሩ ሌሎች ምሳሌነቱን እንዲከተሉ የሚያደርግ ሰው ነው::

ጳውሎስ ሁልጊዜም ኢየሱስ ክርስቶስን ሊመስለው ይመኛል፤ ስለዚህ «ቢሆንልኝ በሞቱም» (ፊል 3:11) ይላል:: ክርስቶስንም ስለሚከተል «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል» (1ቆሮ 11:1) ይላል:: ክርስቶስን መምሰል ማለት ክርስቶስ መሆን ማለት አይደለም፤ የክርስቶስን ባሕርይ በሙላት እየያዙ ወደ እርሱ ማደግ ማለት ነው:: የተሰሎንቄ ሰዎች ክርስቶስን ይመስሉ ነበር (1ተሰ 1:6) እንደተባለላቸው ሁሉም አማኝ እግዚአብሔርን ሊመስል ተጠርቶአል (ኤፌ 5:1)፤

ከአንድ መንፈሳዊ መሪ ሕዝቡ የሚጠብቀው አነስተኛ ነገር አርአያነት ነው:: ያለዚያ ተከታይ የሌለው ሰው ይሆናል:: በምሳሌነት የሚመሩ መሪዎች ውጤታማ ናቸው:: ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች «...እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ» (2ተሰ 3:9) ብሎ እንደተናገረው «እኔን ምሰሉ» (1ቆሮ 11:1) የሚለው አገላለጽ በተግባሩ የማያፍር መሪ የሚናገረው ቃል ነው::

ምሳሌነት የሚተላለፍ ነው:: በመቄዶንያና በአካያ ላሉት ምዕመናን የተሰሎንቄ ሰዎች ምሳሌ ሆነውላቸው ነበር (1ተሰ 1:7):: የተሰሎንቄ ሰዎች ደግሞ በይሁዳ የሚኖሩትን በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን የእግዚአብሔር ማኅበሮች መስለው ነበር (2:14)::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳንኤል ሲናገር:- «ከአምላኩ ሕግ በቀር ምንም ሰበብ አልተገኘበትም» (ዳን 6:4) እንደሚል እንዲሁ የወንጌል አገልጋይ በኑሮው በገንዘብ አያያዙ፤ በአስተዳደሩ፤ በውጭ ባሉት (በኅብረተሰቡ ዘንድ) ሳይቀር ባለው አካሄድ ሰበብ ወይም ነቀፋ የሌለበት የክርስቶስን ባሕርይ ለዓለም የሚያሳይ መሆን ይገባዋል::





እንዲሁም በቅዱሳን መካከል ከግብዝነት የጸዳ ሕይወት መኖር ይገባል:: በአጠቃላይ በምሳሌነት መምራት ከመሪ የሚጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት ነው::

## 7. ጳውሎስ ለታመኑ ሰዎች አደራ የሚሰጥ መጋቢ::

ሐዋርያው ጳውሎስ ተተኪ ማዘጋጀትንና አደራ ማስተላለፍን በትጋት ያደረገ ሰው ነው:: «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ:: ...መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶኛል» (1ቆሮ 9:16-17) በማለት የተሰጠውን ወንጌልን የመስበክ አገልግሎት መፈጸም እንደሚገባው ይገልጻል:: እንዲሁም ጳውሎስ ከእርሱ አደራ የሚቀበሉትን ጢሞቴዎስን፤ ቲቶን፤ አፍሮዲጡን ሌሎችንም ያዘጋጀ፤ ያለማመደና ያሠማራ አስተማሪ ነው:: ጳውሎስ ተተኪዎችን ከሚያለማምድበት መንገድ አንዱ ሰዎቹ ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን በቅርበት መከታተል ነው:: ለምሳሌ ስለ ቲቶ ሲናገር «በቲቶ ልብ ስለ እናንተ ያንን ትጋት የሰጠ» (2ቆሮ 8:16) ይልና «ስለ እናንተ በጸሎት ይጋደላል» (ቆላ 4:12) ይላል::


የወንጌል አገልግሎት በዘመን ያልተገደበ የማያቋርጥ ተግባር በመሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ አለበት:: ከዚህ አንጻር ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችም ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ» (2ጢሞ 2:2) በማለት ያዘዋል:: ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለሀያ ዓመታት ያህል በቅርበት ያውቀዋል:: በስድስቱ የጳውሎስ መልእክቶች ጢሞቴዎስ በተባባሪ ጸሐፊነት ተጠቅሶአል::

ወንጌልን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ተቀባዮቹ «የታመኑ ሰዎች» ሊሆኑ ይገባል:: መታመናቸው የተቀበሉትን የወንጌል አደራ

እነርሱም በተራቸው እንደተቀበሉት አድርገው ለሌሎች ማስተላለፍ ወይም ማስተማር መቻላቸው ነው።

በአንዳንዶች ዘንድ ተተኪ አገልጋዮችን ማዘጋጀት «ራስን ከሥራ እንደ ማስወጣት»[26] ተደርጎ ይቆጠራል። ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ጊዜ መሪ የነበረው ሲለቅ ሥራውንና አሠራሩን የተለማመደ ተተኪ ሳይኖር ይቀራል። ጳውሎስ ግን ተተኪዎችን መረጠ፤ አስተማረ፤ አለማመደ። ለምሳሌ ቲቶን ከራሱ ጋር ካቆየው በኋላ

## አደራን የማስተላለፍ ሰንሰለት




በቀርጤስ የተወው በዚያ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያደራጅና ሽማግሌዎችን እንዲሾም ነበር (ቲቶ 1:5)።

እንግዲህ ዘላለማዊው እግዚአብሔር ዘመናትን የሚያልፍና ቀጣይነት ያለው እቅድ እንዳለው የሚረዳ አገልጋይ ሞት ሳይቀድመው የራሱን የአገልግሎት ድርሻ በትጋት ፈጽሞ ለተተኪዎች ያስረክባል።

---

[26] To work oneself out of a job





### 8. ጳውሎስ ሙሉውን ሰው ለማገልገል የሚተጋ መሪ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል ሰባኪነቱ እጅግ የበረታ ትጉህ አገልጋይ መሆኑ ይታወቃል። እንዲሁም ለሚያገለግላቸው ሰዎች ኑሮ የሚያስብና የሚጠነቀቅ ሰው ነበር። ሥራ ፈትነትን የሚጠላ ሰዎች በራሳቸው እጅ ሠርተው የሚያስፈልጋቸውን እንዲያሟሉ የሚመክርና ይህም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሥርዓት ሆኖ እንዲጠበቅ ያዘዘ ሐዋርያ ነው (2ተሰ 3:6-13)። ከዚሁም ጋር በኢየሩሳሌም ራብ በነበረበት ዘመን በሌሎች አካባቢዎች ከነበሩ ቅዱሳን ገንዘብን በመሰብሰብ እርዳታ ይዞ ሄደ (ሐዋ 11:29)።

በአንድ አገር በሚኖሩ ቅዱሳን መካከል ችግር (ራብ) ሲኖር በሌላ አገር የሚኖሩት እንዲረዷቸው እርዳታ እንዲሰበሰብ ጳውሎስ ይመክራል (1ቆሮ 16:1-2፤ 2ቆሮ 8:1-9:15)። ምንም እንኳን በተለያየ ሀገር የሚኖሩ ቢሆኑም በቅዱሳን መካከል ለሚኖረው መረዳዳት ምክንያት አድርጎ የሚያስተምራቸው እርስ በርስ ያላቸው «መንፈሳዊ አንድነት» ነው። ከአሕዛብ ወገን ያመኑት «በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች» (ሮሜ 15:26) እንዲረዱ ሲመክር «አሕዛብ በእነርሱ መንፈሳዊ ነገርን ተካፋዮች ከሆኑ በሥጋዊ ነገር ደግሞ ያገለግሉአቸው ዘንድ ይገባቸዋልና» (15:27) በማለት የእርስ በርስ መደጋገፍን ያስተምራል። እንዲሁም አማኞች እንደ ችሎታቸው መጠን አዋጥተው በይሁዳ ለሚኖሩት ወንድሞች እርዳታን ሲልኩ እርዳታውን ያደረሰው ጳውሎስ ነበር (ሐዋ 11:30)።

መንፈሳዊ መሪዎች ለመንጋው መንፈሳዊ ሕይወት መጠንቀቅ ቀዳሚ ተግባራቸው ነው። እንዲሁም ሰው ሥጋ፤ ነፍስና መንፈስ በመሆኑ ስለሚበሉት፤ ስለሚጠጡትና ስለሚለብሱት ማሰብ ራሳቸውንም እንዲረዱ ማስተማርና ማገዝ የተሟላ አገልግሎት[27]

---

[27] Holistic Ministry

መስጠት ነው:: በአጠቃላይ መሪዎች አንዱ የሌላውን ሸክም እንዲሸከም (ሮሜ 15:1፤ ገላ 6:2) ማስተማርና በዚህ ረገድ ራሳቸውም ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል::

## 9. ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት የሚከተል የወንጌል አገልጋይ::

ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል ሰባኪነት ሦስት የአገልግሎት (የሚሲዮን) ጉዞዎችን አድርጓል:: በአገልግሎቱም ከሐዋርያት ጋር ተመካክሯአል (ሐዋ 15:1):: የቤተ ክርስቲያን አዕማድ የሆኑትንም ሄዶ አግኝቷል፤ አነጋግሯል፤ ምክር ጠይቋል (ገላ 2):: እንዲሁም እርሱ አብዝቶ እየጸለየ ሌሎች አማኞችም እንዲጸልዩለት ይጠይቅ ነበር (ሮሜ 15:30-32):: በዚህ ሁሉ አደራን እንደተቀበለ የወንጌል አገልጋይና «እንደ ባለ አዕምሮ» ያስባል፤ ይጸልያል፤ ያቅዳል፤ ይንቀሳቀሳል:: ይህ ሁሉ ሆኖ ሐዋርያው ጳውሎስ ዕቅዱን «ክፍት» አድርጎ ይጠብቅ የነበረ:: በዕቅዱና በሀሳቡ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሀሳብ ሌላ ቢሆን ዕቅዱን ለመቀየር ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነበር::

በሁለተኛው የአገልግሎት ጉዞአቸው እስያ ከደረሱ በኋላ «ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው» (ሐዋ 16:6) አልተናገሩም:: ወደ ቢታንያ ለመሄድ ሲፈልጉ የኢየሱስ መንፈስ አልፈቀደላቸውም (16:7):: እዚህ ላይ ልብ እንበል እነዚህ ሰዎች እስከ ምድር ዳር ድረስ በመሄድ ቃሉን እንዲናገሩ በሐዋ 1:8 ላይ አጠቃላይ ሰማያዊ ፈቃድ አግኝተዋል:: ስለዚህ የትም በመሄድ ወንጌልን መስበክ ይችላሉ (ይገባቸዋል):: «እስከ ምድር ዳርቻ» (ሐዋ 1:8) ድረስ እንዲሄዱ «አጠቃላይ» ትእዛዝ የሰጠ ጌታ «እኔ ...ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ 28:20) ብሏልና አብሮ ያለው አለቃ ለየእለቱ የሥራ ስምሪት ይሰጣል:: ይህን ጳውሎስ በውል ስለተረዳ ለምሳሌ ወደ ቆሮንቶስ መሄድ ፈልጎ «...ጌታ ቢፈቅድ ፈጥኜ ወደ እናንተ እመጣለሁ» (1ቆሮ 4:19) ይላል::





ሥራው የራሱ የመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ የሚያውቅና አገልግሎት ማለትም ከእርሱ ጋር ተስማምቶ ማገልገል መሆኑን የተገነዘበ ሰው ሲፈቀድለት ለመሄድ፤ ሲከለከል አቅጣጫን በመቀየር ወደ ተፈቀደለት ለመዞር ራሱን የሚያዘጋጅ ነው:: በመንፈሳዊ ሥራ የአገልግሎት እቅድ ትርጉም የሚኖረው ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት ሲኖር ነው:: እቅዱ ከተዘጋጀ በኋላ እግዚአብሔር ዕቅዱን ሊቀይረው ቢወድ የተቀየረውን እቅድ ፈጥኖ መቀበል ነው:: ምክንያቱም እኛ «ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» (1ቆሮ 3:9):: እንግዲህ ክርስቲያናዊ መሪ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ሁሉ የእርሱን ፈቃድና ምሪት የሚከተል መሆን ይኖርበታል::

## 10. ጳውሎስ ለሙሉ ደምወዝ የሚሠራ የእግዚአብሔር ባሪያ::

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አገልግሎትና ደምወዝ ሲናገር:- «እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር:: እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ አንዳች አይደለም:: የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደምወዝ ይቀበላል» (1ቆሮ 3:6-8) ይላል:: አገልግሎትን በተመለከተ ጳውሎስና አጵሎስ «አንድ ናቸው»:: ደምወዝ ግን የሚቀበሉት እያንዳንዳቸው በነጠላ ነው::

ጳውሎስና አጵሎስ «አንድ ናቸው» ማለትም አንድን ዓላማ የሚያገለግሉ የጌታ ባሪያዎች ናቸው:: ይሁን እንጂ እነርሱ ደግሞ «አንዳች አይደሉም» እግዚአብሔር የመረጠው ከሰዎች ጋር መሥራትን ስለሆነ እንጂ ያለ እነርሱም ቢሆን ሥራው ሊሠራ ስለሚችል «ምንም» አይደሉም:: ሆኖም ቸር እግዚአብሔር ለጳውሎስ፣ ለአጵሎስና ለአገልጋዩቹ ሁሉ እንደ ቸርነቱ ብዛት

ደምወዝ ይከፍላል፡፡ «ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደምወዙን ይቀበላል» (3፡14) እንደተባለ፡፡

ጳውሎስ ለአገልግሎቱ ዋጋን ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር፤ በምድር ሳይሆን በሰማይ ይጠብቅ ነበር፡፡ ስለሆነም ናፍቆቱን ሲገልጽ «በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ»[28] (ፊል 3፡14) ይላል፡፡ ይህ «ምልክት» ወይም «ግብ» ኢየሱስ ክርስቶስን መመልከት ነው (ዕብ 12፡2)፡፡

ጳውሎስ ሙሉ ደምወዝን ስለሚጠባበቅ ራሱን በራሱ ይመዝናል (ይነስማል)፤ ወደ ወንድሞች ቀርቦ ምክር ይጠይቃል፤ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል፡፡ ወደ ዋኖች ወንድሞች በመቅረብ ያደረገውን ሲናገር «...ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው ዋኖች መስለው ለሚታዩ ለብቻቸው አስታወቅኋቸው» (ገላ 2፡2) ይላል፡፡ ይህ በጥንቃቄ መሄድና በጥሩ አጨራረስ ለመፈጸም የሚፈልግ ሰው ነው፡፡ በመጨረሻም «መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፤ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» (2ጢሞ 4፡7-8) በማለት ስለሚጠብቀው ሙሉ ደምወዝ ይናገራል፡፡ የሐዋርያው ጳውሎስ ሩጫ ወንጌልን የመስበክ ሩጫ ነው (ሐዋ 20፡24)፡፡

መንፈሳዊ ሕይወት እንደ ሩጫ ነው፡፡ የሩጫ ሕግ አለው፡፡ የሩጫው ሕግ እግዚአብሔርን በመፍራት የእርሱን ሀሳብ በማገልገል እና በተሰመረለት የአገልግሎት መስመር ውስጥ ማገልገል ነው፡፡ ሕጉን ጠብቆ ሩጫውን ለሚጨርስ በመጨረሻው

[28] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፡ «እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፡ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ» (3፡14)፡፡





ከክርስቶስ ሽልማት ይቀበላል (2ጢሞ 4፡8)፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን መሪ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ከመቅረቡ በፊት በምድር እያለ ራሱን ሊያይ፤ በወንድሞቹም ራሱን ሊያስመረምር፤ ራሱንም አስተካክሎ ሩጫውን ሊፈጽም ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ለአክሊል (ለሙሉ ደምወዝ) ያበቃል፡፡

በአጠቃላይ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ግልጽ ዓላማ ያለው፤ በተጠራበት አገልግሎት በመስጠት ያገለገለ፤ «እለት እለት የሚከብደኝ የቤተ ክርስቲያን ሸክም ነው» (2ቆሮ 11፡23) እንዳለው ትኩረቱ የእግዚአብሔር ሥራ የሆነለት ሰው ነበር፡፡ ጳውሎስ የከበረውን ከተዋረደው፤ ዘላለማዊውን ከጊዜያዊው ለይቶ ስላወቀ በደረሰበት ብዙ መከራ፤ መታሰርና ግርፋት ሁሉ የጸና የወንጌል አርበኛ ነው፡፡ ጳውሎስ ወደ ፊት የሚጠብቀውን ክብር ታላቅነት በማየት በምድር ያለውን ስም፤ ዝና፤ ክብር ሁሉ ለወንጌል ሲል እንደ ጉድፍ በመቁጠር ራሱን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ የሰጠ ትሑት መሪ ነው፡፡

እንዲሁም ለጳውሎስ ሕይወትና ትንሹም ትልቁም አገልግሎት ለእግዚአብሔር ክብር ነው፡፡ «እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት» (1ቆሮ 10፡31)። ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር ማድረግ አምልኮና ስግደት ክብርና ውዳሴ ለሚገባው ለሕያው እግዚአብሔር የምናቀርብለት የሰርክ መሥዋዕታችን ነው፡፡

ስለዚህ በዚህ ዘመን የምንገኝ አገልጋዮች ከሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወትና አገልግሎት የምንማረው ብዙ ነው፡፡

ምዕራፍ 8

# ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና መሪነት ለመማር ከሌሎች ሰዎች ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ተወዳድሮ በዚህ መጽሐፍ መቅረቡ አግባብነት ያለው አይመስልም:: ሌሎች ማለትም ዮሴፍ፤ ሙሴ፤ ዳዊት፤ ነህምያ፤ ኢዮስያስ፤ ሕዝቅያስ፤ ጴጥሮስ፤ ጳውሎስ ሁሉም ፍጡሮች ናቸው:: ሁሉም ደካሞች ናቸው:: ጌታ ኢየሱስ ግን እርሱ አምላክና ፍጹም ሰው ነው::

ከእነዚያ ሕይወትና አመራር በርካታ ትምህርቶችን እናገኛለን:: እግዚአብሔር ይጠብቀን እንጂ በእነርሱ የታዩ ተመሳሳይ ድክመቶች በእኛ ሊደገሙ ይችላሉ:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፍጹም ሰው ነው:: እርሱ ኃጢአትን አላደረገም (1ጴጥ 2:22):: እንደ እኛ የተፈተነ ቢሆንም እርሱ በፈተናችን ሁሉ ሊረዳን የሚችል ሊቀ ካህናችን ነው (ዕብ 4:15):: ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ አንድም ምሳሌያችን ነው፤ ደግሞም እርሱ የሚረዳንና የሚራራልን ሊቀ ካህናት ነው:: ከአካሄዱ በመማርና ምሳሌውን በመከተል ልንመስለው እንፈልጋለን:: በዚህም ጎዳና ሊቀ ካህናችን ነውና ስንደክም ወደ እርሱ እንጮሃለን፤ ይራራልናል፤ ያማልድልናል፤ ያግዘናል:: ስሙ ይባረክ::





ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም በይሁዳ ቤተ ልሔም ተወለደ:: የእርሱን መወለድ ይጠብቁ ለነበሩ እረኞች ታወጀ (ሉቃ 2:8-20):: በቤተ ልሔም ይሁዳ የተወለደው ኢየሱስ ያደገው በገሊላ ናዝሬት ነበረ:: ስለዚህም «የናዝሬቱ ኢየሱስ» (ዮሐ 1:45) ተብሎ ይጠራል::

ከድንግል ማርያም የተወለደው የናዝሬቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ማቴ 1:23፤ 28:19፤ 2:15፤ 3:17፡ 14:33፡ 16:16፡ 27:54)፤ የተቀባ ነው (ሐዋ 4:26-28)፤ የንጉሥ ዳዊት ልጅ ሲሆን (ሉቃ 1:30፤ ማቴ 22:42) የንጉሥ ዳዊት ጌታም ነው (22:41-45)፤ የአይሁድ ንጉሥ ነው (2:2፤ 27:37)፤ መላእክት ይታዘዙለታል (13:41፤ 16:27፤ 24:30-31፤ 26:53)፤ ኃጢአትን ይቅር ይላል (9:2-8)::

ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በይፋ የጀመረው በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ በውኃ ከተጠመቀ በኋላ ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ፤ ድንቅና ተዓምራትንም እያደረገ፤ በሽተኞችን እየፈወሰ፤ በአጋንንት የተያዙትንም ነጻ እያወጣ ይዞር ነበር:: ሕዝቡ ሊረዳው (ሊገነዘበው) በሚችለው አገላለጽና በምሳሌም ያስተምራቸው ነበር::

ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም የምሥራች የሆነውን የመንግሥት ወንጌል በተለያየ መንገድ ማለትም በመግለጽ፤ በመተንተን፤ በማስጠንቀቅ፤ በማጽናናት፤ በመምከር አስተማረ:: ጌታ ኢየሱስ ያስተማረው በቤተ መቅደስ (ዮሐ 8:2)፤ በምኩራብ (ሉቃ 4:16)፤ በመንገድ (ማር 10:17)፤ በሰዎች ቤት (ሉቃ 14:1)፤ ለትልቅ ጉባኤ (ሉቃ 5:1-3)፤ እንደ ኒቆዲሞስ ለአንድ ሰው (ዮሐ 3)፤ ለወንዶችና ለሴቶች (ሉቃ 8:1-3) ለሰው ሁሉ ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተል ብዙ ሕዝብ ነበር:: ከእነዚህ መካከል አስራ ሁለቱን መረጠ፤ ደቀ መዛሙርት ብሎ ጠራቸው:: ከእነርሱም ጋር ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ያስተምርና በሽተኞችንም ይፈውስ ነበር:: ሕዝብ ተከማችቶ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ሆነው ሲያገኛቸው ያዝንላቸው፤ ያስተምራቸው የሚበሉትንም ይሰጣቸው ነበር (ማቴ 9:35)::

ይህን ያዩ አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ንጉሥ ሊያደርጉት የፈለጉበት ጊዜ ነበር:: ኢየሱስ ግን እነርሱ የፈለጉትን ዓይነት ንጉሥ ለመሆን አልወደደም (ዮሐ 6:15):: ንጉሥ ኢየሱስ በከብቶች በረት ከመወለድ አንስቶ አኗኗሩና ትምህርቱ ሰዎች እንደሚፈልጉት አልነበረም:: ካህናት፤ አለቆችና ብዙኀኑ እንዲያደርግ የሚፈልጉትን የሚፈጽም አልሆነላቸውም::

ብዙዎች እንደተከተሉት ያዩ የካህናት አለቆች ይቀኑበትና ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር:: ጻፎች፤ ፈሪሳውያንና ሕግ አዋቂዎች ይፈትኑት ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለሁሉም እውነትን እያስተማረ ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል በምድር ላይ ተመላለሰ::

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ሆኖ በገባ ጊዜ ብዙዎችን አስደነቀ:: ወደ ቤተ መቅደስም በመግባት ቤተ መቅደሱን አጸዳ:: «የአባቴ ቤት የጸሎት ቤት ይባላል» (ኢሳ 56:7) እንደተባለው ቤቱን ከለዋጮችና ከነጋዴዎች አጸዳ (ዮሐ 2:13-17)::

ሊገድሉት አጥብቀው ይፈልጉት የነበሩ የካህናት አለቆች በፋሲካ በዓል ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የነበረው ይሁዳ አሳልፎ እንዲሰጣቸው ገንዘብ ቆጠሩለት:: ይሁዳም በሰላሳ ብር አሳልፎ ሸጠው:: የእግዚአብሔር በግ የሆነው ጌታ ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ያደርግ ዘንድ በመስቀል ላይ መከራን ተቀበለ፤ ሞተ:: በመስቀልም





ላይ ሆኖ የመጣበትን ዓላማ ስለ ጨረሰ «ተፈጸመ» (ዮሐ 19:30) ብሎ ተናገረ::

ኢየሱስ ክርስቶስ ገና በምድር እያለ እንደ ተናገረው በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ:: ለደቀ መዛሙርቱም ታየ:: «ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው» (ሐዋ 1:3)::

ኢየሱስ ክርስቶስ በየዘመናቱ የሃይማኖት መሪዎች ነን ብለው በምድር ላይ ከተነሱት ሰዎች ሁሉ ፈጽሞ የተለየ መሪ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ[29] መሪ የሆነው:-

## 1ኛ. በማንነቱ:-

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ፤ ፍጹም ሰው ነው:: እንዲህ ፍጹም መለኮት እና ፍጹም ሰው የሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር አልነበረም፤ የለም፤ አይኖርም::

## 2ኛ. በባሕርዩ:-

ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአት ያላደረገ ፍጹም ሰው ነው:: በዚህ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የተለየ ነው:: ሌሎች መሪዎች ሁሉ ሰዎች በመሆናቸው ኃጢአተኞች ናቸው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ኃጢአት የለበትም::

## 3ኛ. በትንሣኤው:-

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱ ልዩ ነው:: ተመልሶ እንዳይሞት ሆኖ ከሞት የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ሌሎች መሪዎች ሁሉ ሞተዋል፤ እንደ ሞቱም ቀርተዋል:: ኢየሱስ

[29] Not only special but unique

ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ አስቀድሞ በነቢያት ተነገረ፤ ከተነሣም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱና ለብዙዎች ታየ፤ ወደ ሰማይም ዐረገ::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሪነቱ ፍጹም ነው:: በየትኛውም ዘመንና የሥልጣኔ ደረጃ ቢሆን የእርሱ አመራር በፍጹምነቱ ምሳሌ ነው:: የእርሱን ምሳሌ (ፍሊጋውን) በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ሁሉ ልንከተል ይገባናል:: ስለሆነም ለክርስቲያናዊ መሪነት ከፍተኛው[30] ምሳሌ አድርገን የምንወስደው የጌታችንን ሕይወትና አመራር ነው:: ከዚህ አንጻር ከአመራር ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ጥቂት ነጥቦች ልብ ማለት ጠቃሚ ነው::

## 1. ጌታ ኢየሱስ ተልዕኮውን የሚያውቅ መልእክተኛ::

ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር ለምን እንደ መጣ በግልጽ ያውቃል:: ከአብ ዘንድ የተሰጠው ሥራ ነበረው (ዮሐ 17:4):: የመጣው ኃጢአተኞችን ለመጥራት (ሉቃ 5:32)፤ ሕይወት ለመስጠት (ማር 10:45፤ ዮሐ 10:16)፤ የመንግሥትን ወንጌል ለመስበክ (ሉቃ 4:43)፤ የጠፉትን ለመፈለግና ለማዳን (ሉቃ 19:10) እንደሆነ ተናግሯል:: ስለሆነም ግልጽ የሆነ ተልዕኮና ዓላማ አለው:: የኖረውም ይህን ዓላማውን በመግለጽ፤ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመጥራትና ተልዕኮውን በመፈጸም ነው (ዮሐ 4:34፤ 6:29፤ 9:4፤ 20:21):: ጌታ ኢየሰስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበትን ዓላማ ያውቃል፤ ከዚህም ዓላማ ዝንፍ አላለም::

ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት ሆኖ ሳለ የህማም ሰውና ሰቃይ ያልተለየው ነበር[31] (ኢሳ 53:3):: መከራን የተቀበለው ስለ እኛ

[30] The ultimate

[31] A man of sorrows and familiar with suffering





ነው:: «እርሱ የእኛን ደዌ ተቀበለ፤ የእኛን ህማም ተሸከመ» (ኢሳ 53:4):: የእኛን ኃጢአት ተሸከመ (1ጴጥ 2:24)፤ ስለ እኛ መተላለፍ ቆሰለ (ኢሳ 53:5)፤ ስለ እኛም በደል ደቀቀ (ኢሳ 53:5)፤ ስለ እኛ መተላለፍ ተወጋ:: ይህ ሁሉ በእርሱ መድቀቅ፤ በእርሱ መወጋት እኛ ጤንነት እንድናገኝ በእርሱ ቁስል እንድንፈወስ ነው (ኢሳ 53:5):: ይህ ተልዕኮው ነው::

መንፈሳዊ መሪ ተልዕኮውን የሚያውቅ የዓላማ ሰው መሆኑ በጣም አስፈላጊ ነው:: ዓላማ ያለው ሰው በሕይወቱ ቀዳሚ የሆነውን ነገር ለይቶ የሚያውቅና ለዚያም የሚያስፈልገውን ዋጋ ለመክፈል የቆረጠ ሰው ነው:: ክርስቲያናዊ መሪ እግዚአብሔር ለሰጠው መልእክት (አገልግሎት) መልእክተኛ ነውና ከሚልከው ከእግዚአብሔር በጥሪው ውስጥ እርሱ ላለበት ዘመንና ቦታ (ስፍራ) ምን ተግባር እንዲያከናውን እንደ ታዘዘ ለይቶ ማወቅ ይጠበቅበታል:: በአገልግሎት ዘመኑም ያን ተልእኮውን በጥንቃቄ ለመፈጸም የሚተጋ ሰው መሆን አለበት::

## 2. ጌታ ኢየሱስ በሰማይ የሚሠራውን እያየ በምድር ያከናወነ መሪ::

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ጎልቶ የሚታየው አንዱ ነገር የላከውን የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ መትጋቱ ነው:: ጌታ በዮሐ 5:19-20[32] ሲናገር:- «...እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ

[32] በአዲስ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ:- «እውነት፤ እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና:: አብ ወልድን ስለሚወድ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፤ ትደነቁም ዘንድ ከእነዚህም የሚበልጥ ነገር ያሳየዋል» ይላል::

ያደርጋልና:: አብ ወልድን ይወዳልና፤ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል»[33] አለ:: በሰማይ ያለውን አይቶ መሥራት ወይም ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ተረድቶ ያንኑ መፈጸም ከጌታ ሕይወት የምንማረው ታላቅ የመሪነት ባሕርይ ነው::

እግዚአብሔርን በማክበር ለመኖር ዓላማው ያደረገና ከእርሱ ለመስማት ፈቃደኛ የሆነ አገልጋይ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው:: ለዚህ ዓይነት አገልጋይ እግዚአብሔር ሀሳቡን ሊገልጽለት (በእርሱ ዘንድ ያለውን ሊያሳየው) ይወዳል ማለት ነው:: ስለሆነም በክርስቲያናዊ መሪነት ከፍተኛውን ደረጃ[34] በእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆነውን እያዩ (ማለትም እርሱን እየሰሙ) መሥራት ነው:: ይህ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ መሥራትን፤ የእርሱ አገልጋይ መሆንን በጉልህ ያሳያል:: የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል ማለትም ይኸው ነው::

[33]ስለዚህ ጥቅስ ትርጓሜ ጨለማም አላሸነፈውም ከሚለው መጽሐፍ የሚከተለውን እናገኛለን:: «በዚህ ላይ ሁለት ጐልተው የሚወጡ ሃሳቦች አሉ፡- 1. ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ 2. አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ያደርጋል:: አብ የሚያደርግውን ሁሉ ወልድ ካደረገ፤ ወልድ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው:: በችሎታ መበላለጥ የሌለበትን እኩልነት ያሳያል:: ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አለመቻሉ በእኩልነት ያለ አንድነትን ያመለክታል:: ይህም አብና ወልድ ሁለቱም አንድ ባሕርይ (አንድ ሃሳብ) እንዳላቸው ያሳየናል:: *አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል (5(20)፡-* ይህ በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነትና እኩልነት ይገልጻል:: *አብ ወልድን ይወዳልና* ሲል አብና ወልድ የእርስ በእርስ ኅብረታቸው በፍጹም ፍቅር ላይ የተመሠረተ፤ አንድነታቸው በፍቅር የተያያዘ እንደሆነ ያሳየናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱን ፈቃድ በሙሉ የፈጸመው ከእርሱ ጋር በነበረው ኅብረትና የእርስ በርስ ፍቅር የተነሣ ነው:: *የሚያደርገውን ሁሉ* ሲል ደግሞ *ሁሉ* ሙሉነትን ወይም ፍጹምነትን ያመለክታል:: ይህም በሙሉ ለወልድ ያሳየዋል ማለት ነው:: ይህም እኩል ማወቅን ያመለክታል::» መልሳቸው መስፍን (1998)፤ ጨለማም አላሸነፈውም፡- የዮሐንስ ወንጌል

[34] Ultimate leadership





### 3. ጌታ ኢየሱስ ቃሉና ተግባሩ የሚመሳሰል መሪ::

ሉቃስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እድገት ሲጽፍ «ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር» (ሉቃ 2:52) አለ:: የተሟላ እድገት በሰው ፊት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም ፊት የሆነ እንደሆነ ነው::

በኤማሁስ መንገድ የነበሩት ደቀ መዛሙርት «በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ» (ሉቃ 24:13-19) በማለት ይናገሩ ነበር:: እዚህ ላይ እንደተገለጠው የኢየሱስ ክርስቶስ «ብርታት» በሥራና በቃል ነበር:: እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስ «ብርታት» በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ነበር:: ይህ ነው ንግግርና ተግባር የተስማሙበት ሕይወት::

ይህ በቃልና በተግባር የተመሳሰለ ሕይወት መኖር ከመሪዎች የሚጠበቅ ትልቅ ባሕርይ ሲሆን በፈሪሳውያን ሕይወት ግን ያልታየ ነገር ነበር:: ስለዚህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 23:2 «ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል፤ ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፤ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ» ብሎ አስተማረ:: ፈሪሳውያን ቃሉን ይናገራሉ፤ የቃሉን ትክክለኛ ትርጉም ግን አያስተውሉም:: የተቀመጡበት ወንበር የሥልጣን ወንበር ነው:: የሚናገሩት እንደ ሕጉ ትክክል ነበር:: ነገር ግን የሚኖሩት ከሚናገሩት ተቃራኒ ስለ ነበረ ጌታ ሕዝቡን ያዘዛቸው የሚናገሩትን አድርጉ ሥራቸውን ግን አታድርጉ ብሎ ነው::

የተናገሩትን በተግባራቸው የሚሸሩ መሪዎች «ዕውር መሪዎች» ስለሆኑ የሚመሩትን ሕዝብ ወደ ገደል ይወስዳሉ:: በማቴ 23:16-24 ስለ «ዕውሮች መሪዎች» ጌታ ሲናገር «ዕውርን ዕውር ቢመራው ተያይዘው ወደ ገደል ይወድቃሉ» (ማቴ 15:14) አለ:: «ዕውር

መሪዎች» በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ የተጻፈውን የማያደርጉ፣ ዋናውን ትምህርት የማይኖሩበት ነገር ግን ለራሳቸው ሥርዓት የሚገዙ ናቸው:: ጌታም «...ከአዝሙድና ከእንስላል ከከሙንም አሥራት ስለምታወጡ፤ ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተው ወዮላችሁ፤ ሌላውን ሳትተው ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር፤ እናንተ ዕውሮች መሪዎች» (ማቴ 23:23) ብሎ ተናግሮአል::

እንግዲህ በወንበር የተቀመጡ መሪዎችና አስተማሪዎች እውነት የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል የሚናገሩ ብቻ ሳይሆኑ የሚናገሩትን በመኖር (በሥራቸው) የሚመሰክሩ ሊሆኑ ያስፈልጋል:: መልካም ምሳሌነትም የሚያስተምሩትን በመኖር ሕዝቡን ወደ መልካም መምራት ነው::

## 4. ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔርንና የሚመራውን ሕዝብ የሚወድ መሪ::

ጌታ ኢየሱስ ሕዝቡ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጥለው ባያቸው ጊዜ አዘነላቸው፤ አስተማራቸው የሚበሉትንም ሰጣቸው (ማቴ 9:36):: ሰውን ሁሉ መውደዱን በርኅራኄ ገለጸ:: እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በመስቀል ላይ አሳልፎ እንዲሰጥ ያደረገው ምክንያት ፍቅር ነው:: እርሱን የሚከተል ሰው ሁሉ ከእርሱ ጋር የሚያያይዘው የማይበጠሰው «ገመድ» ፍቅር ነው::

ጌታ ኢየሱስ ወደ አባቱ መሄጃው ሲደርስ «በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻው ወደዳቸው» (ዮሐ 13:1):: እርሱም ደቀ መዛሙርቱን «እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ» (13:34) አለ::





የእርስ በርስ መዋደድ በጌታ ደቀ መዛሙርት መካከል ልዩ ምልክት፤ መለዮ ወይም ዓርማ ነው:: የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሆኑት ከሌላው ሕዝብ የሚለዩት ልዩ በሆነ አለባበሳቸው ወይም አካሄዳቸው አይደለም:: የጌታ የሆኑት ዋና ምልክታቸው የእርስ በርስ መዋደዳቸው ነው:: በምድር ካሉት ማናቸውም ኅብረቶች ሁሉ ክርስቲያኖችን ልዩ የሚያደርጋቸው የወንድማማች መዋደድ ነው:: ይህ በዓለም የሚታወቁበት ምልክታቸው ነው:: ይህንን ፍቅር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመኖር አሳይቶታል::

«ፍቅር» እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር የላከበት ምክንያት ነው (ዮሐ 3:16):: እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ በአገልግሎት የሚሠማሩበት ምክንያት ፍቅር ሊሆን ይገባል:- የክርስቶስ የመስቀል ፍቅር:: ይህም ጳውሎስ «የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና» (2ቆሮ 5:14) እንዳለው` ማለት ነው:: እንዲሁም መሪዎች በአገልግሎት የሚሠማሩበት እግዚአብሔርንና የሚያገለግሉትን ሕዝብ ስለሚወዱ መሆን አለበት:: ክርስቲያናዊ አመራርን ከሌሎች ክርስቲያናዊ ካልሆኑ አመራሮች ልዩ የሚያደርገው ይህ ፍቅር ነው:- እግዚአብሔርን በመውደድ የሚያገለግላቸውንም ሰዎች መውደድ ነው:: ጌታም ትእዛዛቱን ሁሉ «ጌታ አምላክህን ...ውደድ፤ ...ባልንጀራህን ...ውደድ» (ማቴ 22:34-40፤ ማር 12:28-34) በማለት ወደ ሁለት ጠቅልሎአቸዋል::

## 5. ጌታ ኢየሱስ ትልቅነት ማለት አገልጋይነት መሆኑን በተግባር ያሳየ መምህር::

ጌታ ኢየሱስ ሁሉም በእግሮቹ ሥር የተገዙለት ጌታ ነው (ዮሐ 13:3):: እርሱ ጌታ ሆኖ ሳለ የኖረው ግን እንደ አገልጋይ ነው:: ትልቅነት ማለት አገልጋይነት እንደሆነ በኑሮው ገለጸ:: የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ በምሳሌነት አሳየ (ዮሐ 13:4-17)::

ለደቀ መዛሙርቱም የነገራቸው እርሱ እግር እንዳጠበ እነርሱም እግር እንዲያጥቡ ነው፡፡ ይህም «አገልጋይነት» የሁልጊዜ ልብሳቸው እንዲሆን ነው፡፡[35]



ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ጌታ ነው፤ መምህር ነው፤ እንዲሁም አገልጋይ ነበረ፡፡ ይህ የባሪያን መልክ የወሰደው ጌታ የማበሻ ጨርቅ ወስዶ የደቀ መዛሙርቱንም እግር አጠበ፡፡ መቼም ለአራት ከተቀመጡት ሰዎች መካከል እግር የማጠብ ተግባር የመምህሩ አይሆንም፡፡ እዚያ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ እርሱ የሌሎችን እግር እንዲያጥብ አይጠበቅም፡፡ ጌታና መምህር የሆነው ኢየሱስ «ለባሪያ/ አገልጋይ» የሚተውን *ሥራ* በመ*ሥራት* የመሪነትን ምንነት በተግባር አስተማረ፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና መምህር ነው፡፡ ከፍተኛው የማዕረግ (ሥልጣን) ደረጃ ላይ እያለ ሌላ ምን ይጠብቃል? ምን

[35] "Jesus calls us, not to a single act but to a single altitude that may manifest itself in many different ways. in our day it may mean taking out the trash, cleanings bathrooms, or changing diapers. 'Foot washing' translates in to performing lowly tasks that every one else avoids because of pride." Kenneth Boa, ibid, p.224.





ይጎድልበታል? ለምን እግር ያጥባል? ሹመት ለማግኘት? ለክብር? አይደለም፡፡ ከዚህ የምናስተውለው ግን አገልግሎት ለዕድገት ሳይሆን አገልግሎት ራሱ ዕድገት መሆኑን ነው፡፡ ትልቅነት ማለት ማገልገል ወይም ማገልገል ትልቅነት መሆኑን ነው፡፡ ጌታ እንዳደረገው ማድረግ ብጹዕነት (መባረክ) ነው፡፡

ጌታን በሚከተሉት ደቀ መዛሙርት መካከል ማን ትልቅ እንደ ሆነ እርስ በእርስ የተከራከሩበት ጊዜ ነበር (ማር 9፡33-49፤ ሉቃ 22፡24-30)፡፡ ጌታም «ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤» (ማቴ 20፤ 26-27፤ ማር 9፡35) አላቸው፡፡ ይህንንም ሕፃን ይዞ በመካከላቸው በማቆም አስረዳቸው፡፡

1ኛ. ሕፃንን እንደ ምሳሌ በመውሰድ *ታናናሾችን በጌታ ስም የሚቀበልና የማያሰናክል ያ* ትልቅ እንደሆነ (ማር 9፡36-37) አስተማረ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሕፃናት ጥበበኞች ወይም ታላላቅ የሚባሉ ሰዎች ወዳሉበት ስፍራ አይጠሩም፡፡ በእነርሱ መካከል ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች አይደሉም፡፡ ጌታ በምሳሌ እንዳስተማረው ግን ህፃናትን የሚቀበል፤ የሚያቅፍ፤ የሚያቀርብ ሰው እርሱ እውነተኛ ትልቅ ሰው እንደሆነ ነው፡፡ ህፃናትን ማቅረብ ማለት የማይጠቅሙ የሚባሉትን መቀበል እነርሱንም ማገልገል ነው፤ ይህ ትሕትና ይጠይቃል፡፡

2ኛ. ከእርሱ «ቡድን» ውጭ የሆኑትን አገልጋዮች የማይነቅፍና የማያርቅ ይልቁን የጌታ የሆኑትን የሚወድ (9፡38-41) ይህ ትልቅ ሰው ነው፡፡ ትልቅነት በጌታ ስም የሚያገለግሉትን ሁሉ መቀበልም ነው፡፡ በጌታ ስም የሚያገለግሉትን ሁሉ የሚቀበል መሪ የጌታ የሆኑ ግን «ሌሎች» የሚባሉትን ለማቅረብ የሰፋ ልብ ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተል ማንኛውንም ሰው ማክበርና አለማሰናከል ትልቅነት ነው፡፡

3ኛ. ትልቅ ሰው ራሱን የሚገዛ ሰው ነው:: እግዚአብሔርን በመፍራት የሚኖር፤ ራሱን በመጎሰም ክርስቲያናዊ ዲሲፕሊን የሚጠብቅ ሰው ነው::

አገልጋይ-መሪ እንደ ሕፃን ትሑትና ቅን ሊሆን ይገባል:: ክርስቲያናዊ መሪ የሕዝበ አገልጋይ ነው:: መሪ እንደ ኢየሱስ ለሚመራቸው ምሳሌ የሚሆን የእግር ማበሻ ታጥቆ የሚያገለግል ነው::

## 6. ጌታ ኢየሱስ ትሑት ጌታ::

ቃል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ሰውን ለማዳን የሰውን ሥጋ በመውሰድ[36] በባሪያ መልክ መምጣቱ የትሕትናው ከፍተኛ መግለጫ ነው:: ከፊል 2:6-9 እንደምንገነዘበው የኢየሱስ ክርስቶስ ትሕትና የተገለጠው ቢያንስ በ3 መንገዶች ነው::

1. የባሪያን መልክ በመውሰዱ መለኮታዊ ክብርን ተወ
2. ለአባቱ በመታዘዙ ሁልጊዜ ፈቃዱን ለማድረግ ተጋ
3. እግዚአብሔር ከፍ እስኪያደርገው ድረስ እርሱን ጠበቀ

ጌታ በምድር ላይ በተመላለሰበትም ጊዜ «ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና» (ማቴ 11:29) በማለት አስተምሮአል:: ትሕትና በውጭ ከሚገለጸው የበለጠ የውስጥ (የልብ) ጉዳይ ነው::

እንዲሁም «እነሆ ንጉሥሽ ...ትሑትም ሆኖ በአህያም፤ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል» (ዘካ 9:9፤ ማቴ 21:5) ተብሎ በነቢዩ ዘካርያስ እንደ ተነገረው ንጉሡ

[36] Incarnation





ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ:: በዚህም ገርነቱን፤ ትሕትናውን አሳይቷል:: ሐዋርያው ጳውሎስም በ2ቆሮ 10:1 «እኔም ራሴ ጳውሎስ በእናንተ ዘንድ ፊት ለፊት ሳለሁ ትሑት የሆንሁ ከእናንተ ግን ብርቅ የምደፍራችሁ በክርስቶስ የዋህነትና ገርነት[37] እመክራችኋለሁ» በማለት ስለ ጌታ ኢየሱስ የዋህነትና ገርነት ይመሰክራል::

ገርነት ደካማነት፤ የራስን መብት አለማወቅ ወይም መፍራት አይደለም:: ገርነት ግን ራስን መግዛት፤ ለበቀል አለመነሳሳት፤ የራስን መንፈስ መግዛት፤ በመከራ ውስጥ መታገስ ነው:: ገር የሆነ ሰው በሆነ ባልሆነው «መብቴ ለምን ተነካ? ክብሬ ተወሰደብኝ!» በሚል አይቆጣም፤ አገልግሎቱን አያቆምም፤ አይበቀልም:: ገር ሰው በቀል የእግዚአብሔር እንደሆነ ስለሚያውቅ (ሮሜ 12:19) ኃይልና ሥልጣን እያለው ይታገሣል፤ አይዝትም::

ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ጌታ ኢየሱስ «...ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ» (1ጴጥ 2:23) አለ:: መልእክቱን የሚጽፍላቸውንም ሲመክር «በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና::

[37] የዋህነትና ገርነት - Meekness - gentleness. "Meekness" is more in the mind internally; "gentleness" in the external behavior, and in relation to others; for instance, the condescending yieldingness of a superior to an inferior, the former not insisting on his strict rights" JFB. "The meek ... an inward quality, as related primarily to God. The equanimity, mildness, kindness. ...The Christian meekness is based on humility, which is not a natural quality but an outgrowth of a renewed nature", Vincent's Commentary on the Greek New Testament.

ኃጢአት አድርጋችሁ ስትነሰሙ ብትታገሡ ምን ክብር አለበት?» (2፡19-21) ይላቸዋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥ ነው፤ መምህር ነው፤ ጌታ ነው፡፡ ትሑቱ ኢየሱስ በሰዎች መካከል ሳያበላልጥ ሁሉንም ሰው አገለገለ፡፡ እርሱ ድሆችንና የተጣሉትን ይወዳል፡፡ ድሆች ፈልገውት አልተሰወረባቸውም፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰበከላቸው፤ ፈወሳቸው፤ አብሮአቸው በላ፡፡ የመጣሁት ኃጢአተኞችን ለመጥራት ነው አለ (ሉቃ 5፡31-32)፡፡ ሰው ዝም የሚያሰኛቸውን ህፃናትና ዕውሮች ‹ተውአቸው ወደ እኔ ይምጡ› አለ፡፡ በቀራጭ ዘኬዎስ ቤት እራት በላ (19፡1-10)፤ አመንዝራዋን ይቅር አለ (7፡36-48)፡፡ ሳምራውያን (9፡51-56፤ 10፡29-37) አቀረበ፤ አባካኙን መልሶ ገንዘቡ ያደርጋል (15፡11-32)፤ ለምጻሞችን ፈወሰ (17፡11-19)፤ ነፍሰ ገዳዩን ይቅር አለ (23፡39-43)፡፡ በኅብረተሰብ ለተናቁት ለመበለቶች፤ ለሴቶች፤ ለእረኞች ሁሉ ግድ ይለው ነበር፡፡

እንግዲህ ክርስቲናዊ መሪ ገር የሆነ፤ ባለው ሥልጣን ተመክቶ የማይዝት፤ ሰውን ሁሉ እኩል የሚያገለግል ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይህንም ከጌታችን እንማራለን፡፡ ትሕትና መሪ ሊያወልቀው ያልተፈቀደለት የሰርከ ልብሱ ነው፡፡

## 7. ጌታ ኢየሱስ ተልዕኮውን ጨርሶ «ተፈጸመ» ያለ መሪ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበትን ዓላማ እንዳይፈጽም ብዙ መሰናክሎች ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ በሰው ዓይን መልካም የሚመስሉ ናቸው፤ ሌሎቹ ደግሞ ከተልዕኮ የሚያደናቅፉ መከራዎች ናቸው፡፡

በሰው ዓይን መልካም መስለው ከቀረቡት ችግሮች አንዱ ሕዝቡ እርሱን ሊያነግሡት መፈለጋቸው ነው (ዮሐ 6፡15)፡፡ አዎ! ኢየሱስ





ክርስቶስ ንጉሥ ነው፡- የዘላለም ንጉሥ ነው፡፡ ሆኖም ወደ ምድር የመጣው በሰዎች መካከል ለመንገሥ አልነበረም፡፡

በሌላ ሁኔታ ደግሞ ጌታ በፊቱ ስለሚጠብቀው ሞት በተናገረ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል «አይሁንብህ» (ማቴ 16፡22) ያሉትና በመስቀል እንዳይሞት ሊከላከሉ የሞከሩ ነበሩ፡፡ እርሱ ግን የአባቱን ፈቃድ በመፈጸም እግዚአብሔርን ለማክበር ወሰነ፡፡

እነዚህ ሁሉ መልካም የሚመስሉ «ምኞቶች» ናቸው፤ ነገር ግን ከተልዕኮ አንጻር የሚያደናቅፉ ነበሩ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያልተሰጠውን ተልዕኮ በማከናወን ለመታወቅ አልፈለገም፡፡ ሰዎች እንዲሆን የተመኙለትንም አልሆነም፤ አባቱ የፈቀደለትን ብቻ ለማድረግ ወሰነ፤ ይህ ነው ተልዕኮን መፈጸም፡፡

ጌታን ከመጣበት ዓላማ የሚያደናቅፉ ብዙ ችግሮችም ነበሩ፡፡ ብዙዎች ነቅፈውታል፡፡ «ጋኔን አለብህ» (ዮሐ 7፡20) ያሉት፤ የጠሉት (5፡1-16)፤ እንደ ከፉ አድራጊም የቆጠሩት (18፡30) ነበሩ፡፡ እርሱ ግን «ነውርን ንቆ፤ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ...» (ዕብ 12፡2) ተልዕኮውን ፈጸመ፡፡ በመስቀልም ላይ ሆኖ የመጣበትን ዓላማ ስለ ጨረሰ «ተፈጸመ» (ዮሐ 19፡30) አለ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሩጫን በትዕግሥት የመሮጥና ተልዕኮን የመፈጸም ምሳሌያችን ነው፡፡

እንግዲህ መሪነት ዓላማን ማወቅ ብቻ ሳይሆን የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ መፈጸምም ነው፡፡ የውጤታማነት መለኪያው ተልዕኮን ዳር በማድረስ እንደ ጌታ «ተፈጸመ» ማለት ሲቻል ነው፡፡

## 8. ጌታ ኢየሱስ የጠፋውን የሚፈልግ መልካም እረኛ፡፡

ጌታ ኢየሱስ የጠፋውን ስለ መፈለግ በምሳሌ ብዙ አስተምሮአል፡፡ በሉቃ 15 ውስጥ ጌታ ስለ ጠፋው በግ፤ ስለ ጠፋው ድሪም፤ ስለ ጠፋው ልጅ ተናግሮአል፡፡ ከምሳሌው እንደምንረዳው ለእያንዳንዱ ለጠፋው ነገር ፈላጊ ነበረው (15፡4፤8፤20)፡፡ በዚህም የጠፋውን መፈለግ አስፈላጊ የእረኝነት ተግባር መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

የጌታ አመራርና ጥበቃ ያተኮረው በቁጥር ብዛት ወይም በአብላጫ[38] ላይ ሳይሆን በነፍስ ወከፍ ጥንቃቄ በማድረግ ላይ ነበር፡፡ በበረት ውስጥ ካሉት በጎች አንዱ ቢጠፋ ከዘጠና ዘጠኙ አንጻር ‹ምንም› ባልሆነ ነበር፡፡ ጌታ ግን ለአንዱ የሚጠነቀቅና እስኪያገኘው ድረስ የሚፈልግ እረኛ ነው፡፡

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረና ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲያደርግ የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት በመሆኑ ከአምላኩ ርቆ ሊባዝንና ሊጠፋ አይገባውም ብሎ ፍለጋ መሄድ የእረኝነት ባሕርይ ነው፡፡ እረኛ በበረት «የቀረው ይበቃኛል» የሚል ሳይሆን አንዱን የጠፋውን ፍለጋ እንደሚሄድ «ሁሉም ለጌታ ያስፈልጉታል» (ማቴ 18፡12፡14) የሚል ሰው ነው፡፡  ክርስቲያናዊ መሪ በተሰማራበት ቦታ ሁሉ ለሰው ዋጋ የሚሰጥ፤ ለአንድ ለባዘነ፤ ለደከመ፤ ለጠፋ ግድ የሚለው ነው፡፡ በአንጻሩ ደካሞችን የሚያገል (የሚያሸሽ) ወይም በመጥፋታቸው የሚደሰትና ጥቂቶቹን ብቻ በታጠረ በረት ውስጥ ቆልፎ የሚይዝ መሪ የመልካሙ እረኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ልብ ያለው አይደለም፡፡

ጌታ ሲናገር «በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ» (ዮሐ 10፡27) አለ፡፡ እንዲሁም ስለ መልካም እረኛ ሲያስተምር፡- «በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፤ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል፡፡

[38] Percentage





የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፡፡ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና» (ዮሐ 10፡3-5) አለ፡፡ ይህ በእረኛና በበጎቹ መካከል ያለውን መተዋወቅ፤ መቀራረብ፤ መተማመን ይገልጻል፡፡ እንዲሁ መሪ የሚመራውን ሕዝብ የሚያውቅ ሕዝቡም በአመራሩ በመተማመን የሚከተለው መሆን አለበት፡፡

የመልካሙን እረኛ የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌነት የሚከተል እረኛ በጎቹን በስም የሚያውቅና ከበረት የጎደሉም ሲኖሩ እንዲመለሱ ፈጥኖ የሚፈልግ ነው፡፡ በጎቹም ወደ በረት እንዲመለሱ አስቀድመው የመሪውን ድምጽ የሚያውቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስለሆነም በመሪውና በተመሪዎች መካከል፤ በእረኛውና በበጎች መካከል የቀረበ ግንኙነትና ትውውቅ አስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ መሪነት መልካም እረኝነት የሚሆነው የጠፋው በተገኘ ጊዜ፤ የባዘነው በተመለሰ ጊዜ፤ የደከመው በተጽናና ጊዜ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መሪ የክርስቶስ ልብ ያለው የባዘኑትን ፈልጎ የሚያገኝ ደስታውም በመመለሳቸው የሚሆንለት ሰው ነው፡፡


## 9. ጌታ ኢየሱስ በአብ የተላከ፤ ሌሎችን ያሰለጠነና የላከ መሪ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎቱ ዘመን ብዙዎች ይከተሉት ነበር (ማር 3፡7-20)፡፡ ዓሣ አጥማጆችን አግኝቶ «በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ አላቸው» (ማቴ 4፡19)፡፡ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት የመረጣቸው፡- «ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው...» (ማር 3፡14) ነበር፡፡ መጀመሪያ የጠራቸው ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፤ እንዲያስተምራቸው፤ እርሱን በቅርብ እንዲያዩት እና ከሕይወቱ እንዲማሩ ነው፡፡ «ተከተሉኝ»

ብሎ ጠርቶ «አደርጋችኋለሁ» ሲል የጌታ ኢየሱስ አመራር ሰውን በመለወጥና በማስቻል ላይ ያተኮረ መሆኑን እናስተውላለን።

ጌታ የመረጣቸው ደቀ መዛሙርት ባሕርያቸውና የሥራ ልምዳቸው ተመሳሳይ አልነበረም። የተለያየ ባሕርይ፣ ልምድና ችሎታ ነበራቸው። ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ ካደረገ በኋላ ትኩረታቸው አንድ አቅጣጫ እንዲይዝ አደረገ፣ ይህም በእርሱ እንዲያምኑ (ዮሐ 6:29) የሕይወታቸውም ቀዳሚው ነገር የእግዚአብሔርን መንግሥት መፈለግ እንዲሆን አስተማራቸው። ይህንም በራሱ ሕይወት አለማመዳቸው። ከዚያም «ጌታ ሌሎችን ሰብዓ ሾመ፤ ሁለት ሁለት አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው። አላቸውም:-...» (ሉቃ 10:1-2) ይላል። ሁለት ሁለት እያደረገ በመላክ ያለማምዳቸው ነበር።

የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት
ማቅረብ - ማስተማር - ለአገልግሎት መሰማራት








ከሦስት ዓመት ተኩል አገልግሎት ጊዜ ውስጥ አብዛኛውን ያሳለፈው ከአሥራ ሁለቱ ጋር በመሆን፣ ለአገልግሎት በማዘጋጀትና ኃላፊነት በመስጠት ነበር።[39] ደቀ መዛሙርት መረጠ፣ አስተማረ፣ አለማመደ። ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ በአብ እንደ ተላከ እርሱ ደግሞ ደቀ መዛሙርትን ላከ።

ጌታ እንደ ፊልጶስ እርሱን በትክክል ያልተረዱትን በማገዝ፣ እንደ ጴጥሮስ «አይሁንብህ» በማለት ከመንገድ ለማስቀረት የሚፈልጉትን በመምከርና በመገሰጽ፣ ፈርተው እስከ መስቀል ድረስ ያልተከተሉትን «ሰላም ለእናንተ ይሁን» በማለት እንዲሁም እንደ ቶማስ ትንሣኤውን የተጠራጠሩትን ያምኑ እንዲሆኑ በማገዝ ደቀ መዛሙርቱን አጽንቶአቸዋል። በተደጋጋሚ የካደውን ጴጥሮስን ሳይቀር «ትወደኛለህን? ብሎ» እንደገና በመጠየቅና በማቅረብ አደራ ሰጥቶታል። ተልእኮአቸውን አጥርተው እንዲያውቁ አድርጎ፣ «ሂዱ» (ማቴ 28:18) በማለት አዘዛቸው፤ በመጨረሻም «...ኃይልን ትቀበላላችሁ ...ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋ 1:8) በማለት አረጋገጠላቸው። ጌታ ተከተሉኝ ብሎ ጀምሮ፣ አገልግሎትን አሳይቶና አለማምዶ «ሂዱ» በማለት አሰማራቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ደካማ የሆኑ ሰዎችን በማሳደግ ኃላፊነት ለመስጠት ታላቅ ምሳሌ ነው። ሰዎች በወደቁበት እንዳይቀሩ፣ እርሱ ላሰበው ዓላማ ብቁዎች ይሆኑ ዘንድ በማጽናናት፣ በመደገፍ አሳደጋቸው። ጴጥሮስ በተደጋጋሚ ድካም እንዳለበት የታየ ሰው ነበር። አደራን ከተቀበለ በኋላ ግን በሐዋርያት መካከል ትልቅ መሪ ሆኖ ያገለገለ፣ በድፍረትም ወንጌልን የሰበከ ሐዋርያ ሆኗል።

[39] "The Son of God invested the vast majority of His time with twelve, not twelve hundred. Jesus practiced the axiom: More time with less people equals greater kingdom impact." The Maxwell Leadership Bible, p.1238.

መንፈሳዊ መሪ ሁሉንም አማኝ የጌታ ደቀ መዛሙርት የሚያደርግ፤ ጥቂቶቹን ደግሞ እርሱ የተቀበለውን ተልዕኮ እነርሱም እንዲቀበሉና የታመኑ ሆነው እንዲሠሩ የሚያስተምርና የሚያለማምድ ሰው ነው:: መሪ ሥራውን ለታመኑት አደራ የሚሰጥ ነው::

10. ጌታ ኢየሱስ ጽድቅን የወደደና አመፃን የጠላ ጻድቅ::
የዕብራውያን ጸሐፊ ዳዊት የተናገረውን በመጥቀስ «...ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ» (ዕብ 1፡9፤ መዝ 45፡7) ይላል::

ጽድቅን መውደድና ዓመፃን መጥላት በጽድቅ የሚኖር ሰው ባሕርይ ነው:: ለጽድቅ ይቆማል፤ ግብዝነትን፤ አመፃን ደግሞ ይቃወማል:: ጌታ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነው:: በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ መገኘት የሌለበትን አስወጣ (ዮሐ 2፡13-15)::

የሰውን የውስጥ ባሕርዩን ከሚገልጡት ነገሮች አንዱ የሚያስቆጣው ነገር ምንነት ነው:: ጌታን ያስቆጣው የቤተ መቅደሱ መርከስ ነበር:: ክርስቲያናዊ መሪ ሆኖ የእግዚአብሔር ቤት በቅድስና መጉደል ሲቆሽሽ የማይቆጣ ከሆነ ከጌታ ኢየሱስ ይህንን ባሕርይ አልወሰደምና መሪ ሊሆን አይገባውም::

11. ጌታ ኢየሱስ የሚጸልይ መሪ::
ጌታ ኢየሱስ «ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ» (ማር 1፡35):: ደቀ መዛሙርቱን በመረጠ ጊዜ ጸለየ (ሉቃ 6፡12-16)፤ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር አብሮ





ይጸልያል (ሉቃ 9፡28-36)፤ ስለ ጸሎትም አስተምሯል (ሉቃ 14፡1-9)::

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጸልይ መሪ ነበር:: መጸለይ እግዚአብሔርን መውደድንና በእርሱ መታመንን መግለጫ መንገድ ነው:: ጌታ በመጨረሻዋ ሰዓት ስለ ደቀ መዛሙርቱ እምነት (ዮሐ 17፡11-12)፤ ስለ ወደፊቱ ሁኔታቸው (13-14)፤ ስለ ፍሬያማነታቸው (18-20)፤ ስለ አንድነታቸው (21-23) ሁሉ ጸለየላቸው:: ኃላፊነትን መስጠት ብቻ ሳይሆን ይጸልያላቸውም ነበር::

ከጸሎት ጋር በተያያዘ የሉቃስ ወንጌልን ብቻ ብንመለከት ኢየሱስ ሲጠመቅ (3፡21)፤ ደቀ መዛሙርቱን ሲመርጥ (6፡12)፤ ለብቻው (11፡1-13; 18፡1-14; 21፡36)፤ በጌቴሴማኒ ተንበርክኮ (22፡39-46)፤ በመስቀል ላይ (23፡46) ጸለየ:: በጸሎት ስለ መትጋት (11፡5-13)፤ ከመጸለይ ስላለመታከት (18፡1)፤ ተቀባይነት ስላለው የጸሎት ዓይነት (18፡9-14) አስተማረ:: ለደቀ መዛሙርቱ (22፡31-32)፤ ለራሱ (22፡41-44)፤ ለጠላቶቹ (23፡34) ጸለየ:: ጸሎት የጌታ የኑሮው ክፍል ነበር:: ስለ ጸሎት በምሳሌዎች አስተማረ:: ደቀ መዛሙርቱን እንዴት እንደሚጸልዩና ተግተው እንዲጸልዩ አስተማረ (6፡28፤ 11፡2-10፤ 18፡1-4):: የመከሩ ጌታ ሠራተኞች እንዲልክ (10፡2)፤ ቤቱ የጸሎት ቤት እንደሆነ (19፡46) ተናገረ:: ጸሎትን ለሰዎች ለመታየት ስላለማድረግ (20፡47)፤ ከመከራ ለመጠበቅ ስለመጸለይ አስተማረ (21፡36)::

ጸሎት ወደ እግዚአብሔር መቅረብና እግዚአብሔርን ወደ ሥራው መጋበዝ ነው:: ጸሎት ለመንፈሳዊ መሪ ቀዳሚ ተግባሩ ነው:: ሐዋርያትም ይህንኑ ገልጸዋል (ሐዋ 6፡4):: ጸሎት አብዛኛውን ጊዜ በእልፍኝ ውስጥ (በጓዳ) የሚደረግ (ማቴ 6፡6) ስለሆነ የግል ታማኝነትን ይጠይቃል:: በግልጽ ለሚታየው የመሪነት ውጤት ጉልበቱ ይህ በጓዳ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረገው ኅብረት ነው::

ፈጽሞ የተማረ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ የሚሆን ነው (ሉቃ 6፡40)፡፡ መምህሩ ኢየሱስ ደግሞ ወደ አባቱ የሚጸልይና የጠበቀ ኅብረት ነበረው፡፡ ስለዚህ መሪዎች ሁሉ በጸሎት ሕይወታቸውና በአብ በመታመናቸው ኢየሱስን እንዲመስሉት ተጠርተዋል፡፡

## 12. ጌታ ኢየሱስ ለአብ ፈጽሞ የታዘዘ ልጅ፡፡

መታዘዝ[40] የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማድመጥን፤ መገንዘብን ሲሆን በተለይ በአክብሮት (በፍርሃት) መስማትን ነው፡፡ ቃሉ ሰሚው ለተናጋሪው ያለውን አክብሮትና የሚሰማውን ለመፈጸም ያለውን ዝግጁነት አመልካች ነው፡፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ሰው ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን እምነትና አክብሮት እንዲሁም ኅብረት ያመለክታል፡፡

ነቢዩ ሳሙኤል ንጉሥ ሳኦልን «መታዘዝ ከመሥዋዕት፤ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል» (1ሳሙ 15፡22) ሲለው እግዚአብሔርን መታዘዝ ከፍ ያለ የኅብረት ደረጃ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም ጌታ እግዚአብሔር አብርሃምን «የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ፤ ቃሌን ሰምተሃልና» (ዘፍ 22፡18) እንዳለው እግዚአብሔርን መስማት (ማለትም መታዘዝ) የበረከት ምንጭ መሆኑን እናስተውላለን፡፡

የመታዘዝ ታላቅ ምሳሌያችን የሆነው ጌታ ኢየሱስ «ለሞትም፤ ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ» (ፊል 2፡8)፤ እርሱም «ለሚታዘዙት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው» (ዕብ 5፡9)፡፡ እንዲሁም መጽሐፍ «አምላኬ ሆይ፤ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ» (ዕብ 10፡7፤ መዝ 40፡7) ይላል፡፡ በተጨማሪም

[40] ó-bē´di-ens, ó-bā´ (Hb:shāma ; Gk: hupakoē):





«የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና» (ዮሐ 6፡38) እንደሚል ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ ነው፤ አደረገውም፡፡

ለእግዚአብሔር መታዘዝ ክርስቲያናዊ መሪ ለአምላኩ ያለውን መወደድና ታማኝነት የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡ መታዘዝ ለበለጠ ክብር ያደርሳል፡፡ ይህ የመታዘዝ ምስጢር ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚለውን የሚሰማና የሚያደርገው ከክብር ወደ ክብር የሚያድግ ሰው ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ስለ አመራር እውቀት ለማግኘት ትምህርት ቤት ገብቶ መማር፤ በመስኩ ሥልጠና መውሰድ እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ልምድን መቅሰም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው፡፡ ስለ ክርስቲያናዊ መሪነት ከሁለትና ሦስት ሺህ ዓመታት በፊት በመሪነት ላይ የነበሩ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችን ሕይወት፤ አገልግሎትና አመራር ማጥናት ግን ምትክ የማይገኝለት የመማሪያ መንገድ ነው፡፡

እግዚአብሔር ‹አልተማሩም› በተባሉ ሰዎች ታላቅ ሥራ ሠርቶአል፡፡ በትምህርታቸው ዓለምን ገልብጦአል (17፡6)፡፡ አሳዳጅን ሰው ለውጦ ለእርሱ የተለየ የወንጌል አገልጋይ አድርጎታል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያስገነዝበው ክርስትና የሰዎች ጥረት ሳይሆን ሰማያዊ መሆኑንና መስፋፋቱም በመለኮት ኃይል መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ፤ እንድትጠነክር፤ ምድርን በክርስቶስ ትምህርት እንድትሸፍን የሆነው ጠሪያቸውንና ጥሪያቸውን ባወቁ ደካማ ሰዎች በኩል መንፈስ ቅዱስ በሠራው ታላቅ ሥራ ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸው የሙሴ፤ የዳዊት፤ የነህምያና የሌሎችም የአመራር ችሎታና ጥበብ በአሁኑም ዘመን ላሉ መሪዎች

ሁሉ የሚያስደንቅ ነው:: እነዚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያሳለፉት በበረሃ፤ በበግ ጥበቃ፤ በስደትና በመሳሰሉ ቦታዎችና ሁኔታዎች ነበር:: ዛሬ የተደረሰበት የአመራር ትምህርት፤ ሥልጠናና የሙያ ማሻሻያ ኮርስ እነርሱ በነበሩበት ዘመን አልነበረም:: ሆኖም የእነርሱ አመራር እንኳንስ እነርሱ በነበሩበት በዚያ «ጥንታዊ» በሚባል ዘመን ቀርቶ «ዘመናዊ» በሚባለው በአሁኑም ዘመን ቢሆን ያልተደገመና ያልታየ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ ከሆነ ምስጢሩ ምንድን ነው?

ምስጢሩማ ሁሉም በእግዚአብሔር ትምህርት ቤት ገብተው መማራቸውና በመንገዳቸው ሁሉ እርሱን መከተላቸው ነው:: የእነርሱ ዋና አስተማሪያቸው እግዚአብሔር ነበር:: ትምህርት ቤታቸውም ከእርሱ ጋር የሄዱበት መንገድና በሕይወታቸው ያለፉበት ሁኔታ ነው:: በእግዚአብሔር የመሪነት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው እርምጃ (ትምህርት) እግዚአብሔርን ማወቅ፤ እርሱን መፍራትና በመሪነቱ ሥር ማደር ነው:: በዚህ ትህምርት ቤት ውስጥ የእግዘአብሔርን ሀሳብ ስለ መረዳት፤ በእርሱ ስለ መታመንና መገዛት፤ ከእርሱ ጋር አብሮ ስለ መሥራት መማር አለ:: አስተማሪያቸው መንገድን የሚያሳይ፤ እጅን ሰልፍ የሚያስተምር፤ መከናወንንም የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው::

ስለዚህ በእግዚአብሔር ትምህርት ቤት የተማሩ ሰዎችን ሕይወትና አገልግሎት በማጥናት የአመራር ልምድ ማግኘት ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለሚገኙ ክርስቲያናዊ መሪዎች ምትክ አይገኝለትም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ የሚገኘው እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት በምድር ላይ የትም ቦታ አይሰጥም:: እነርሱን ያስተማረና ያሰለጠነ ሕያው እግዚአብሔር ዛሬም አስተማሪና መሪ ነው::

ከዚህ ቀጥሎ ባለው ቅጽ 4 እስካሁን በነበሩት 3 ቅጾች ያየናቸውን የመሪነት ሀሳቦች በማሰባሰብ፤ በማዋሃድና በማጠቃለል በ21ኛው





ክፍለ ዘመን ሊኖር ስለሚገባ ክርስቲናዊ መሪነት እንመለከታለን:: ይህንም በሥዕላዊ መንገድ ጭምር ለማስረዳት አንድ የክርስቲያናዊ መሪነት ‹መንፈሳዊ ቤት› እንሠራለን::

# ዋቢ መጻሕፍት

ከቅጽ ፩ እስከ ቅጽ ፬ ላሉት ቅጾች ሁሉ ዋቢ መጻሕፍቱ ተጠቃለው በቅጽ ፬ ቀርበዋል።

ስለ አመራር እውቀት ለማግኘት ትምህርት ቤት ገብቶ መማር፤ በመስኩ ሥልጠና መውሰድ እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ልምድን መቅሰም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው። ስለ ክርስቲያናዊ መሪነት ግን ከሁለትና ሦስት ሺህ ዓመታት በፊት በመሪነት ላይ የነበሩ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችን ሕይወት፤ አገልግሎትና አመራር ማጥናት ምትክ የማይገኝለት የመማሪያ መንገድ ነው።

የሙሴ፤ የዳዊት፤ የነህምያና የሌሎችም የአመራር ችሎታና ጥበብ በአሁኑም ዘመን ላሉ መሪዎች የሚያስደንቅ ነው። እነዚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያሳለፉት በበረሃ፤ በበግ ጥበቃ፤ በስደትና በመሳሰሉ ቦታዎችና ሁኔታዎች ነበር። ዛሬ የተደረሰበት የአመራር ትምህርት፤ ሥልጠናና የሙያ ማሻሻያ ኮርስ እነርሱ በነበሩበት ዘመን አልነበረም። ሆኖም የእነርሱ አመራር እንኳንስ እነርሱ በነበሩበት በዚያ «ጥንታዊ» በሚባል ዘመን ቀርቶ «ዘመናዊ» በሚባለው በአሁኑም ዘመን ቢሆን ያልተደገመና ያልታየ ነው ማለት ይቻላል።

የዚህ ምስጢሩ ደግሞ ሁሉም በእግዚአብሔር ትምህርት ቤት ገብተው መማራቸውና በመንገዳቸው ሁሉ የእርሱን መሪነት መከተላቸው ነው። የእነርሱ ዋና አስተማሪያቸው እግዚአብሔር፤ ትምህርት ቤታቸውም ከእርሱ ጋር የሄዱበት መንገድና በሕይወታቸው ያለፉበት ሁኔታ ነው። በእግዚአብሔር የመሪነት ማሰልጠኛ ተቋም የመጀመሪያው የትምህርት ኮርስ እግዚአብሔርን ማወቅ፤ እርሱን መፍራትና በመሪነቱ ሥር ማደር ነው። እነርሱን ያስተማረና ያሰለጠነ እግዚአብሔር ዛሬም ሕያው አስተማሪና መሪ ነው።

ለክርስቲያናዊ መሪነት ከፍተኛው ምሳሌያችን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅነት ማለት አገልጋይነት መሆኑን በተግባር ያሳየ መምህር ነው። እርሱ ጌታ ሆኖ ሳለ በምድር የኖረው እንደ አገልጋይ ነው። የክርስቲያን መሪነት «ሙላት» ምሳሌውን በመከተል እርሱን በመምሰል ማደግ ነው።

Designed & Printed @ Andnet Printers

ዋጋ 40 ብር